መዝሙር ፤ ፻፷ ።

፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ነግሠ ፡ ትትሐሠይ ምድር ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ እግዚአብሔር ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሠራ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ደስ ፡ ይላታል ፡ ማለት ፡ የዘሩባትን ፡ ታበቅላለች ፡ የተከሉባትን ፡ ታጸድቃለች ። አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሠርቷልና ፡ ትሩፍ ፡ ደስ ፡ ብሏት ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ትወጣለች ።

ወይትሐሠያ ፡ ደሰያት ፡ ብዙኃት ።

ብዙ ፡ ደሴቶች ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ ማለት ፡ በደሴት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። ወንግር ዎሙ ፡ ሠናይቶ ፡ ለእለ ፡ ውስተ ፡ ደሴት ፡ እንዲል ። አንድም ፡ ደሴት ፡ በወሀ ፡ እንዲከበብ ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ በመከራ ፡ የተከበቡ ፡ ትሩፋን ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ መከራው ፡ ርቆላቸው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

፪ ፤ ደመና ፡ ወቆባር ፡ ዐውዱ ።

ደመና ፡ ጽጋግ ፡ በዙሪያው ፡ አለ ፡ ማለት ፡ በባሕርዩ ፡ ፅኑ ፡ መቅሠፍት ፡ አለ ።

ፍትሕ ፡ ወርትዕ ፡ ተድላ ፡ መንበሩ ።

ፍትሕ ፡ ርትዕ ፡ ምቹ ፡ ዙፋኑ ፡ ናቸው ። ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፲፫ ።

፫ ፤ እሳት ፡ የሐውር ፡ ቅድሜሁ ።

እሳት ፡ በፊቱ ፡ ይሄዳል ፡ ማለት ፡ መቅሠፍት ፡ በባሕርዩ ፡ አለ ።

ወነድ ፡ የዐግቶሙ ፡ ለጸላዕቱ ።

ጠላቶቹን ፡ እሳት ፡ ይከብባቸዋል ፡ ማለት ፡ መቅሠፍት ፡ ያጠፋቸዋል ።

፬ ፤ አስተርአየ ፡ መባርቅቲሁ ፡ ለዓለም ።

መባርቅተ ፡ መዓቱ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ አንድም ፡ ለትሩፋን ፡ (ረድ) ፡ ረዳት ጠበቃ ፡ በመሆን ፡ ተገለጸ ።

ርዕደት ፡ ወአድለቅለቀት ፡ ምድር ።

በዬዋዌ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በሚጠት ፡ ጊዜ ፡ ባቢሎን ፡ ጠፋች ።

ኢሳ ፡ ፷፯ ፡ ፲፭ ።

፭ ፤ አድባርኒ ፡ ተመስዉ ፡ ከመ ፡ ሠምዕ

ነገሥታቱ ፡ እንደ ፡ ሠም ፡ ቀልጠው ፡ ጠፉ ። ኢሳ ፡ ፷፬ ፡ ፪ ።

እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ ገጽ ፡ መዓቱ ከመገለጽ ፡ የተነሣ ።

እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵላ ፡ ምድር ።

የእግዚአብሔር ፡ ገጽ ፡ መዓቱ ፡ ከመገለጽ ፡ የተነሣ ፡ ባቢሎን ፡ መላዋ ፡ ትጠፋለች ። ኢሳ ፡ ፲፫ ፡ ፲፫ ። መዝ ፡ ፻፲ ፡ ፫ ፡ ፯ ።

፮ ፤ ይነግሩ ፡ ሰማያት ፡ ጽድቀ ፡ ዚአሁ ።

ሰማያት ፡ አንድም ፡ መላእክት ፡ ቸርነቱን ፡ ይነግራሉ ፡ ያስተም ራሉ ።

ወኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ርእዩ ፡ ስብሐቲሁ

አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ጌትነቱን ፡ አዩ ፡ አወቁ ።

፯ ፤ ይትኃፈሩ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይሰግዱ ፡ ለ ግ ል ፎ ።

ለተቀረጸ ፡ ለተጎነፈ ፡ ጣዖት ፡ የሚ ሰግዱ ፡ ሁሉ ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ፤ አንድም ፡ አጥብቀህ ፡ ያፍራሉ ፡ ይ ዋረዳሉ ።

ወእለ ፡ ይትሜክሁ ፡ በአማልክቲሆሙ ።

ቤል ፡ ዳጎን ፡ ያድነናል ፡ እያሉ ፡ በጣዖቶቻቸው ፡ የሚመኩ ፡ ሁሉ ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ፡ ያፍራሉ ፡ ይዋ ረዳሉ ።

ወይሰግዱ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎሙ ፡ መላእክቲሁ

እንዲህ ፡ የሚሉ ፡ ሁሉ ፡ ለራሳ ቸው ፡ ይባሳቸው ፡ እንጂ ፡ ለሱስ ፡ መላእክት ፡ ሁሉ ፡ ይሰግዱለታል ፤ ይገዙለታል ። ኢሳ ፡ ፵፪ ፡ ፲፯ ። ዕብ ፡ ፩ ፡ ፮ ።

፰ ፤ ሰምዐት ፡ ወተፈሥሐት ፡ ጽዮን ።

ልዑላኑ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ወተሐሥያ ፡ አዋልደ ፡ ይሁዳ ።

የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ትሑታኑ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

በእንተ ፡ ፍትሕከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ፡አንተ ፡ ስለ ፡ ፈረድህላቸው ፡

፱ ፤ እስመ ፡ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባሕ ቲትከ ፡ ልዑል ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ።

እግዚአብሔር ፡ በ፩ቱ ፡ መዓዝን ፡ ያለህ ፡ ልዑል ፡ አምላክ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህና ፡ መዝ ፡ ፹፩ ።

ፈድፋደ ፡ ተለዓልከ ፡ እምኵሉ ፡ አማልክት

በስመ ፡ አምላክነት ፡ ከሚጠሩ ፡ ሁሉ ፡ ፈጽመህ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አልህ። ኢሳ ፡ ፱ ፡ ፲፩-፲፱ ።

፲ ፤ እለ ፡ ታፈቅርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጽልእዋ ፡ ለእኪት ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምላ ኮ ፡ የምትወዱት ፡ ኃጢአትን ፡ ጣዖትን ፡ ጥሏት ፡ ተዋት ።

የዓቅብ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነፍሰ ፡ ጻድቃኑ

እግዚአብሔር ፡ የትሩፋንን ፡ ሰው ነት ፡ ከመከራ ፡ ይጠብቃልና ።

ወያድኅኖሙ ፡ እምእደ ፡ ኃጥኣን ። ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፱ ። ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፭ ።

ከባለጸጎችም ፡ እጅ ፡ ያድናቸዋልና፡ አንድም፡ ይጠብቃል፡ ያድናቸዋል ፡ ብለህ ፡ እሥር ።

፲፩ ፤ ብርሀ ፡ ሠረቀ ፡ ለጻድቃን ።

ለትሩፋን ፡ ሚጠት ፡ ተደረገላቸው፡ አንድም ፡ ለጻድቃን ፡ ጌታ ፡ ተወለ ደላቸው ።

ወሠርቱዓን ፡ ልብ ፡ ትፍሥሕት ።

ፈጽመው ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ትሑት ፡ ሰብዕና ፡ ላላቸው ፡ ለትሩፋን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ለጻድቃን ፡ ልጅነት ፡ ተሰጣቸው ።

፲፪ ፤ ይትፌሥሑ ፡ ጻድቃን ፡ በእግዚአብሔር

ትሩፋን ፡ አንድም ፡ በቁሙ ፡ ጻድቃን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምነው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ወአምንዩ ፡ ለዝክረ ፡ ቅድሳቱ ። መዝ ፡ ፳፱

ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ተብሎ ፡ ለሚመሰገን ፡ ለስሙ ፡ መታሰቢያም ፡ ይገዛሉ ።

መዝሙር ፡ ፺፯ ።

፩ ፤ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስብሐተ ሐዲሰ ። መዝ ፡ ፺፭ ፡ ፩ ። ፻፵፱ ፡ ፩

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንግዳ ፡ ምስጋና ፡ አመስግኑት ።

እስመ ፡ መንክር ፡ ግብረ ፡ እግዚአብሔር

የእግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ ድንቅ ፡ ነውና ።

ወአድኅኖቱ ፡ የማኑ ።

በሥልጣኑ ፡ የሚያደርገው ፡ ትድግናውም ፡ ድንቅ ፡ ነውና ።

ወመዝራዕቱሂ ፡ ቅዱስ ።

ሥልጣኑም ፡ ፅኑ ፡ ልዩ ፡ ነውና ።

፪ ፤ አርአየ ፡ እግዚአብሔር ፡ አድኅኖቶ ።

እግዚአብሔር ፡ በሰባ ፡ ዘመን ፡ ትድግናውን ፡ ገለጸ ፡ አንድም ፡ ባምስት ፡ ሺሕ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ወልድን ፡ በሥጋ ፡ ገለጸ ።

ወበቅድመ ፡ አሕዛብ ፡ ከሠተ ፡ ኪዳኖ ።

በአሕዛብም ፡ ፊት ፡ ወጅዓም ፡ ሐሊቆን ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ኪዳኑን ፡ አንድም ፡ በአጋንንት ፡ ፊት ፡ በኀሙስ ፡ ዕለት ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ኪዳኑን ፡ ገለጸ ።

፫ ፤ ወተዘከረ ፡ ሣህሎ ፡ ለያዕቆብ ።

ለሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ይቅርታውን ፡ አሰቦ ፡ አንድም ፡ ለያዕቆብ ፡ ዘነፍስ ፡ ይቅርታውን ፡ አሰቦ ።

ወጽድቆሂ ፡ ለቤተ ፡ እስራኤል ።

ቸርነቱንም ፡ ላሥሩ ፡ ነገድ ፡ አንድም ፡ ለእስራኤል ፡ ዘነፍስ ፡ አሰቦ፡

ርእዩ ፡ ኵሉ ፡ አጽናፈ ፡ ምድር ፡ አድኅኖቶ ፡ ለአምላክነ ።

የምድር ፡ ዳርቻ ፡ በምትሆን ፡ ዘቁላተ ፡ ኀዘን ፡ ያላችሁ ፡ ዐሥሩ ፡ ነገድ ፡ አንድም ፡ በነቢብ ፡ በገቢር ፡ ፍዳ ፡ የተያዛችሁ ፡ መላችሁ ፡ የፈጣሪያችንን ፡ ትድግናውን ፡ እወቁ ።

፬ ፡ የብቡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኵሉ ፡ ምድር

ባራቱ ፡ መዓዘን ፡ ያላችሁ ፡ ትሩፋን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡

አቅርቡ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመ ስግኑ ። መዝ ፡ ፷፰ ፡ ፩ ። ፺፱ ፡ ፩ ።

ሰብሑ ፡ ተፈሥሑ ፡ ወዘምሩ ።

ሰብሑ ፡ ወዘምሩ ፡ ወተፈሥሑ ፡ ነው ፡ ደስ ፡ ብሏችሁ ፡ አመስግኑ ፡ ለሱ ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፡ አንድም ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማመስገናችሁ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ።

፭ ፡ ዘምሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በመሰንቆ ።

መሰንቆውን ፡ እየመታችሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ።

በመሰንቆ ፡ ወበቃለ ፡ መዝሙር ።

መሰንቆና ፡ መሰንቆ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ መሰንቆውን ፡ እየመታችሁ ፡ በበገና ፡ ዕቃ ፡ (ቃል) ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ።

፮ ፡ በቀርነ ፡ ዝብጠ ፡ ወበቃለ ፡ ቀርን ።

ሰንተል ፡ ነጋሪትም ፡ እየመታችሁ፡ አንድም፡ተመትቶ፡የተሠራ፡ነጋሪት፡ እየመታችሁ ፡ አንድም ፡ ዝብጡ ፡ ቀርነ ፡ ነጋሪት ፡ ምቱ ፤ አንድም ፡ ተራ ፡ ነጋሪትም ፡ እየመታችሁ ፡

ወየብቡ፡በቅድመ፡እግዚአብሔር፡ንጉሥ

በቤተ ፡ መቅደስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሁሉ ፡ (ቅድመ) ፡ ፊቱ ፡ ሲሆን ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ቅድሙ ፡ ይለዋልና ፡

፯ ፡ ወትትከወስ ፡ ባሕር ፡ በምልዓ ።

የላንትን ፡ ምስጋና ፡ ሰምታ ፡ ባቢሎን ፡ በመላዋ ፡ ትደረጻለች ።

ዓለምኒ፡ወኵሎሙ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስቴታ

ዓለም ፡ በቁሙ ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ። ኢሳ ፡ ፵፬ ፡ ፲፱

፰ ፡ አፍላግኒ ፡ ይጠፍሑ ፡ እደ ፡ ኅቡረ ።

ነገሥተ ፡ እስራኤል ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ወአድባርኒ ፡ ይትሐሠዩ ፡ እስመ ፡ በህየ ፡ ይኬንና ፡ ለምድር ።

በልቡና ፡ በነገር ፡ ለምድር ፡ ይፈርድላታል ፡ በምድር ፡ ይፈርድባታልና ፡ እስራኤልም ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ካሥሩ ፡ ነገድ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ባንድነት ፡ ያመሰግናሉ።

፱ ፡ ወይኬንና ፡ ለዓለም ፡ በጽድቅ ።

ለኢየሩሳሌም ፡ አንድም ፡ ለትሩፍ ፡ በውነት ፡ ይፈርድላታልና ፤ ይፈርድላታል ፡ ላለው ፡ ስጥ ።

ወለአሕዛብኒ ፡ በርትዕ ።

በባቢሎን ፡ አንድም ፡ በአሕዛብ ፡ በውነት ፡ ይፈርድባታልና ፤ ይፈርባታል ፡ ላለው ፡ ስጥ ።

መዝሙር ፡ ፺፯ ።

፩፡እግዚአብሔር፡ነግሠ፡ደንገጹ፡ አሕዛብ

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ እግዚአብሔር ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሠራ ፡ አሕዛብም ፡ ጠፉ ።

ዘይነብር ፡ ዲበ ፡ ኪሩቤል ፡ አድለቅ
ለቃ ፡ ለምድር ።
በኪሩቤል ፡ አድሮ ፡ የሚኖር ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ በዜዋዌ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሩ
ሳሌምን ፡ በሚጠት ፡ ጊዜ ፡ ባቢሎ
ንን ፡ አጠፋት ።
፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ ዐቢይ ፡ በጽዮን ።
በጽዮን ፡ ሰማያዊት ፡ በጽዮን ፡ ምድ
ራዊት ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ገናና ፡ ነው ።
ወልዑል ፡ ውእቱ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ፡አሕዛብ
ከአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ገናና ፡
አምላክ ፡ ነውና ።
፫ ፤ ኵሉ ፡ ይገኒ ፡ ለስምከ ፡ ዐቢይ ።
ሰው ፡ ሁሉ ፡ ገናና ፡ ለሚሆን ፡
ስምህ ፡ ይገዛል ።
እስመ ፡ ግሩም ፡ ወቅዱስ ፡ ውእቱ ።
ዕፁዕ ፡ ከሐሊ ፡ ገናና ፡ ነውና ።
፬ ፤ ክቡር ፡ ንጉሥ ፡ ፍትሐ ፡ ያፈቅር ።
ክቡር ፡ ዘሩባቤል ፡ አንድም ፡ ጌታ ፡
እውነት ፡ መፍረድን ፡ ይወዳል ።
አንተ ፡ አጽናዕከ ፡ ለጽድቅ ፡ በኃይልከ ።
አንተ ፡ ወ፸ ፡ ዓም ፡ ሐሊቆን ፡
ብለህ ፡ ዕለተ ፡ ሚጠትን ፡ በከሀ
ሊነትህ ፡ አፀናኻት ፡ ማለት ፡ እን
ድትፈጸም ፡ አደረግኻት ፡ ፈጸም
ምኻት ።

ፍትሐ ፡ ወጽድቀ ፡ ለያዕቆብ ፡ አንተ ፡
ገብርከ ።
ፍትሐ ፡ ወጽድቀ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡
ለባሪያህ ፡ ለትሩፍ ፡ ሚጠትን ፡ አደ
ረግህለት ፡ ሚክ ፡ ፯ ፡ ፰ ።
፭ ፤ ተለዐለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።
ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ እስራ
ኤልን ፡ አሕዛብን ፡ አጥፍቶ ፡ ልዕ
ልናውን ፡ ገለጸ ።
ወይሰግዱ ፡ ሎቱ ፡ ታሕተ ፡ መከየደ ፡
እገሪሁ ።
ከእግሩ ፡ መመላለሻ ፡ በታች ፡ ለ
ሱ ፡ ይሰግዱለታል ። ኢሳ ፡ ፷ ፡ ፲፬ ።
፮ ፤ እስመ ፡ ቅዱሳን ፡ እሙንቱ ፡ ሙሴ ፡
ወአሮን ፡ በክህነቶሙ ።
ቅዱሳን፡ በክህነቶሙ ፡ ሙሴ ፡ ወአ
ወአሮን ፡ ሙሴ ፡ አሮንም ፡ በክህ
ነታቸው ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸ
ውና ፡ ይሰግዱለታል ። ዘሌ ፡ ፲፰፡ ፩ ።
ወሳሙኤልኒ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ይጼውዑ ፡
ስሞ ።
ሳሙኤልም ፡ ስሙን ፡ ከሚጠሩ ፡
ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ይሰግድለታል ፤ አን
ድም ፡ ሳሙኤል ፡ ወእለ ፡ ይጼውዑ፡
ስሞ ፡ ሳሙኤልና ፡ ስሙን ፡ የሚ
ጠሩ ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ይሰግዱለታል።
ይጼውዕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ውእቱኒ ፡
ይሰጠዎሙ ።
እግዚአብሔርን ፡ ይለምኑታል ፡
እሱም ፡ ልመናቸውን ፡ ይሰማቸ
ዋል ፡ ማለት ፡ የለመኑትን ፡ ያደር
ግላቸዋል ። ዘፀ ፡ ፴፫ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፸፭
፯ ። ዕብ ፡ ፯ ፡ ፪ ።

፯ ፤ ወይትናገሮሙ ፡ በዓምደ ፡ ደመና ።

በረቂቅ ፡ አንድም ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ይነግራቸው ፡ ነበረ ፡ ሳሙኤልን ፡ ወዴት ፡ ተናግሮት ፡ ነበር ፡ ቢሉ ፡ እስራኤል ፡ አባ ፡ ጸሊ ፡ በእንቲአነ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፡ የመብረቅ ፡ የነጐድ ጐድ ፡ ድምፅ ፡ አሰምቷልና ።

መየዐቅቡ ፡ ስምዖ ።

ኢታምልከን ፡ ይጠብቃሉ ።

ወትእዛዞሂ ፡ ዘወሀበሙ ።

የሠራቸው ፡ ፲ኙን ፡ ሕገጋትም ፡ ይጠብቃሉ ።

፰ ፤ እግዚኦ፡አምላክነ ፡ አንተ ፡ ሰማዕኮሙ
አቤቱ ፡ ፈጣሪያችን ፡ አንተ ፡ ልመ ናቸውን ፡ ሰምተኻቸዋልና ።

እግዚኦ ፡ አንተ ፡ ተሣሃልኮሙ ።

አቤቱ፡አንተ፡ይቅር፡ብለኻቸዋልና ።

ወትትቤቀል ፡ በኵሉ ፡ ምግባሮሙ ።

በሥራቸው ፡ ሁሉ ፡ ትፈርድላቸዋ ለህና ፡ ተበቀል ፡ ሊተ ፡ እምዕድ ውየ ፡ እንዲል ።

፱ ፤ ተለዐለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ እስራ ኤልን ፡ አድኖ ፡ አሕዛብን ፡ አጥ ፍቶ ፡ ልዕልናውን ፡ ገለጸ ።

ወይሰግዱ፡ሎቱ፡ውስተ፡ደብረ፡መቅደሱ
መመስገኛው ፡ በምትሆን ፡ ደብረ ፡ መቅደስ ፡ በተሠራችባት ፡ በኢየሩ ሳሌም ፡ ይሰግዱለታል ።

እስመ ፡ ቅዱስ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክነ ።
ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ፅኑዕ፡ ከሐሊ ፡ ነውና ።

መዝሙር ፡ ፺፱ ።

፩ ፤ የብቡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኵሉ ፡ ምድር ። መዝ ፡ ፷፭ ፡ ፩ ። ፺፯ ፡ ፬ ።

በአራቱ ፡ መዓዝን ፡ በምልዓት ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፤ ለሱ ፡ ምሲጋና ፡ አቅርቡ ፡ አንድም፡ ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ መልታችሁ ፡ ያላችሁ ፡ እናንተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ።

፪ ፤ ተቀንዩ፡ለእግዚአብሔር፡በትፍሥሕት
ደስ ፡ ብሏችሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተገዙ ። መዝ ፡ ፲፪ ፡ ፲፩ ።

ወባኡ ፡ ቅድሜሁ ፡ በሐሤት ።

ደስ ፡ እያላችሁ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅ ደስ ፡ ግቡ ።

፫ ፤ አእምሩ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ አምላክነ ።

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ እን ደሆነ ፡ እወቁ ።

ወውእቱ ፡ ፈጠረነ ፡ ወአኮ ፡ ንሕነ ።

እሱ ፡ እንደ ፡ ፈጠረን ፡ እኛ ፡ ፍጠ ረን ፡ እንዳላልነው ፡ አንድም ፡ እር

ስ ፡ በርሳችን ፡ እንዳልተፈጠርን ፡ አንድም ፡ እኛ ፡ እሱን ፡ እንዳልፈ ጠርነው ፡ እሱ ፡ እኛን ፡ እንደ ፡ ፈጠረን ፡ እወቁ ።

ንህነሰ ፡ ሕዝቡ ፡ ወአባግዐ ፡ መርዔቱ ።

እኛ ፡ ግን ፡ ወገኖቹ ፡ ነን ፡ ከዚያ ውም ፡ ዘንድ ፡ የጥንተ ፡ ተገዦቹ ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ ልጆች ፡ ተገዦቹ ፡ ነነ ። ኢሳ ፡ ፵፩ ፡ ፰ ።

፬ ፡ ባኡ ፡ ውስተ ፡ አናቅጺሁ ፡ በተጋንዮ ።

ተግታችሁ ፡ በማመስገን ፡ አንድም፡ በተጋንዮ ፡ ተግታችሁ ፡ ለማመስ ገን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግቡ ።

ወውስተ ፡ አዕጻዲሁ፡በስብሐት ፡ እመንዎ

ከቤተ ፡ መቅደስም ፡ ገብታችሁ ፡ በጥንተ ፡ ምስጋናው ፡ አመስግኑት ፡ እመኖ፡ወልድየ፡እንዲል ። ኤር ፡ ፯ ፡ ፱ ።

፭ ፡ ወሰብሑ ፡ ለስሙ ፡ እስመ ፡ ኄር ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ቸር ፡ ነውና ፡ ለስሙ ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፡ ስሙ ፡ ልዩ ፡ እሱ ፡ ልዩ ፡ ሆኖ ፡ አይ ደለም ፡ ስሙን ፡ እየጠራችሁ ፡ አመ ስግኑት ፡ ማለት ፡ ነው ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

ወለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ ጽድቁ ።

ቸርነቱ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

መዝሙር ፡ ፻ ።

፩ ፡ ምሕረተ ፡ ወፍትሐ ፡ አሐሊ ፡ ለከ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል። ምሕ ረትን ፡ ፍትሕን ፡ ታደርግልኛለህ ፡ ብዬ ፡ (እሴብሕ) ፡ አመሰግናለሁ ።

እዜምር ፡ ወሰሌቡ ፡ ፍኖተ ፡ ንጹሐ ።

ምሕረትን ፡ ፍትሕን ፡ እንድታደር ርግልኝ ፡ አውቄ ፡ አመሰግንሃለሁ ፡ ንጹሕ ፡ ሕግህንም ፡ እጠብቃለሁ ።

፪ ፡ ማዕዜ ፡ ትመጽእ ፡ ኀቤየ ።

ምሕረተ ፡ ወፍትሐ ፡ አኀሊ ፡ ለከ ፡ እዜምር፡ ወእሌቡ ፡ ፍኖተ፡ ንጹሐ ፡ ትላለህ ፡ እንጂ ፡ በኔ ፡ መቼ ፡ ታም ናለህ ፡ አለው ፡ ጌታ ፡ ትሩፋን ።

ወአሐውር ፡ በየዋሀት ፡ ልብየ ፡ ማዕከለ ፡ ቤትየ ።

እኔስ ፡ ኀዳጌ ፡ በቀል ፡ ሁኜ ፡ በወ ገኖቼ ፡ በእስራኤል ፡ መኻል፡ መቼ፡ እኖራለሁ ።

፫ ፡ ወኢረሰይኩ ፡ ቅድመ ፡ አዕይንትየ ፡ ግብረ ፡ እኩየ ።

ካይኖቼ ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ አላ ደረግሁም ፡ ማለት ፡ ላጥፋህ ፡ አላ ልሁም ።

ጸላእኩ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ።
ዓመፅን ፡ የሚሠሩ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ኢኮንያንን ፡ ጠላሁ ፡ አንድም ፡ ጠላሁ ፡ እንጂ ፡ ኢረሰይኩ ፡

፬ ፡ ወኢተለወኒ ፡ ልብ ፡ ጠዋይ ።
ጠማማ ፡ አእምሮ ፡ ያለበት ፡ እኔን ፡ አይመስልም ። አንድም ፡ (ልበ ፡ ጠዋይ) ፡ የጠማማ ፡ የኢኮንያን ፡ የሴዴቅያስ ፡ አንድም ፡ የባቢሎናዊ ፡ ልብ ፡ እኔን ፡ አይመስልም ።

ሶበ ፡ ተማኅው ፡ እኩይ ፡ እምኔየ ፡ ኢያእመርኩ ። ዘበ ፡ ፳፫-፩ ፡ ፫ ።
ኢኮንያን ፡ ሴዴቅያስ ፡ አንድም ፡ ባቢሎናዊ ፡ ጣዖት ፡ ባመለከ ፡ ጊዜ፡ ሳጠፋው ፡ አልወደድሁም ።

፭ ፡ ዘየሐሚ ፡ ቢጾ ፡ በጽሚት ፡ ኪያሁ ፡ ሰደድኩ ።
ወንድሙን ፡ በቀስታ ፡ የሚያማ ፡ ኢኮንያን ፡ ሴዴቅያስን ፡ ከሕይወት ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ከተድላ ፡ ወደ ፡ መከራ ፡ አስወጥቼ ፡ ሰደድሁ ፡ ሰደድሁ ፡ እንጂ ።

ዕቡየ ፡ ዓይን ፡ ወስሱዕ ፡ ልብ ፡ ኢይቀሀወል ፡ ምስሌየ ።
ባይኑ ፡ ብቅና ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ የሚመለከት ፡ ልቡ ፡ ለምግብ ፡ ጣዖት ፡ ለማምለክ ፡ የሚሳሳ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ በረድኤት ፡ አንድ ፡ አይሆንም ፡

፮ ፡ አዕይንትየሰ ፡ ኀበ ፡ መሃይምናነ ፡ ምድር ።
የኔስ ፡ አይኖቼ ፡ በምድር ፡ የታመኑ ፡ ነቢያት ፡ ካህናትን ፡ ይመለከከታሉ ።

ከመ ፡ እንብሮሙ ፡ ምስሌየ ።
በረድኤት ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ አኖራቸው ፡ ዘንድ ፡

ዘየሐውር ፡ በፍኖት ፡ ንጹሕ ፡ ውእቱ ፡ ይትለአከኒ ።
በንጹሕ ፡ ግብር ፡ ፀንቶ ፡ የሚኖር ፡ ካህን ፡ ጽድቁ ፡ ነቢየ ፡ ጽድቁ ፡ ያስተምርልኛል ።

፯ ፡ ወኢይነብር ፡ ማዕከለ ፡ ቤትየ ፡ ዘይገብር ፡ ትዕቢተ ።
ትዕቢተኛ ፡ ኢኮንያን ፡ ሴዴቅያስ ፡ አንድም ፡ ባቢሎናዊ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ በረድኤት ፡ አይኖርም ።

ወኢያረትዕ ፡ ቅድሜየ ፡ ዘይነብብ ፡ ዓመፃ
ዓመፅን ፡የሚናገር፡ ኢኮንያን፡ ሴዴቅያስ ፡ ነገረ ፡ መንግሥቱን ፡ አያቀናም ።

፰ ፡ በጽባሕ ፡ እቀትሎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ኃጥኣነ ፡ ምድር ።
የዚህ ፡ ዓለም ፡ ኃጥአን ፡ ኢኮንያንን ሴዴቅያስን ፡ ሁሉ ፡ ፈርጄ ፡ አጠፋቸዋለሁ ።

ከመ ፡ እሠርዎሙ ፡ እምሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኵሎሙ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ።
የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ከም

ትሆን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ገበርተ ፡
ዓመፃን ፡ ሁሉ ፡ አጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡
አንድም ፡ (ምሕረተ ፡ ወፍትሐ ፡
አኃሊ ፡ ለከ) ፡ ምሕረትን ፡ ፍትሕ
ን ፡ አደርግልሃለሁ ፡ ይላል ፡ ጌታ ፡
ትሩፋን ፡ (እዜምር ፡ ወእሌቡ ፡ ፍ
ኖተ ፡ ንጹሐ) ፡ እኔም ፡ እንጂ ፡ እን
ድታደርግልኝ ፡ አውቄ ፡ አመሰግ
ንሃለሁ ፡ ይላል ፡ ትሩፍ ፡ ጌታችንን ።
(ማዕዜ ፡ ትመጽእ ፡ ኀቤየ) ፡ ምሕ
ረተ ፡ ወፍትሐ ፡ አኃሊ ፡ ለከ ፡ ትላ
ለህ ፡ እንጂ ፡ በረድኤት ፡ ወደኔ ፡
መቼ ፡ ትመጣለህ ። (ወአሐውር ፡
በየውሀተ ፡ ልብየ ፡ ማእከለ ፡ ቤትየ) ፡
እኔስ ፡ ጠላት ፡ ጠፍቶልኝ ፡ ኢየሩ
ሳሌም ፡ ወጥቼ ፡ በዕረፍት ፡ መቼ ፡
እኖራለሁ ። (ወኢረሰይኩ ፡ ቅድመ ፡
አዕይንትየ ፡ ግብረ ፡ እኩየ) ፡ ጣዖ
ትን ፡ አላመለክሁም ። (ጸላእኩ ፡ ገበ
ርተ ፡ ዓመፃ) ፡ ዓመፅን ፡ የሚሠሩ ፡
ባቢሎናውያንን ፡ ጠላሁ ፡ እንጂ ፡ ኢረ
ሰይኩ ። (ወኢተለወኒ ፡ ልብ ፡ ጠዋ
ይ ፡ የኢኮንያንን ፡ የሴዴቅያስን ፡ ልብ ፡
ጠላሁ ፡ እንጂ ፡ ኢረሰይኩ ፡ (ሶበ ፡
ተግሕሠ ፡ ዕኩይ ፡ እምኔየ ፡ ኢያ
እመርኩ) ፡ ነቢየ ፡ ሐሰት ፡ ካህን ፡
ጣዖት ፡ ከኔ ፡ በተለየ ፡ ጊዜ ፡ ጣዖት ፡
አላመለክሁም ። (ዘየሐሚ ፡ ቢፆ ፡
በጽሚት ፡ ኪያሁ ፡ ሰደድኩ) ፡ ወን
ድሙን ፡ በቀስታ ፡ የሚያማ ፡ ኢኮ
ንያን ፡ ሴዴቅያስን ፡ ከሕይወት ፡
ወደ ፡ ሞት ፡ አስወጥቼ ፡ ሰደድሁ ፡
እንጂ ፡ ኢያእመርኩ ። (ዕቡየ ፡ ዓ
ይን ፡ ወስሱዓ ፡ ልብ ፡ ኢይትሀ
ወል ፡ ምስሌየ) ፡ ባይኑ ፡ ብቅና ፡
ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ የሚመለከት ፡ ልቡ ፡
ጣዖት ፡ ለማምለክ ፡ የሚሳሳ ፡ በኔ ፡
ነግሦ ፡ አይኖርም ፡ (አዕይንትየስ ፡
ኀበ ፡ መሃይምናነ ፡ ምድር) ፡ የኔስ ፡
ዓይኖቼ ፡ ነቢያት ፡ ካህናትን ፡ ይመ
ለከታሉ ፡ (ከመ ፡ አንብሮሙ ፡ ምስ
ሌየ) ፡ በመምርነት ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡
አኖራቸው ፡ ዘንድ ፡ (ዘየሐውር ፡
በፍኖት ፡ ንጹሕ ፡ ውእቱ ፡ ይትለ
ዓከኒ) ፡ በንጹሕ ፡ ግብር ፡ ፀንቶ ፡
የሚኖር ፡ ካህን ፡ ጽዱቁ ፡ ነቢየ ፡
ጽድቁ ፡ ያስተምርልኛል ። (ወኢይነ
ብር ፡ ማዕከለ ፡ ቤትየ ፡ ዘይገብር ፡
ትዕቢተ) ፡ ትቢተኛ ፡ ኢኮንያን ፡
ሴዴቅያስ ፡ በወገኖቼ ፡ ነግሦ ፡ አይ
ኖርም ፡ (ወኢያረትዕ ፡ ቅድሜየ ፡ ዘይ
ነብብ ፡ ዓመፃ) ፡ ዓመፅን ፡ የሚና
ገር ፡ ኢኮንያን ፡ ሴዴቅያስ ፡ ነገ
ሩን ፡ መንግሥቱን ፡ አያቀናም ፡
(በጽባሕ ፡ እቀትሎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡
ኃጥአነ ፡ ምድር) ፡ በቀኖና ፡ ዕለት ፡
ዕለት ፡ እየጸለይሁ ፡ አጠፋቸዋለሁ ፡
(ከመ ፡ እሥርዎሙ ፡ እምሀገረ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ለኵሎሙ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ) ፡
የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ከምት

ሆን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ዓመፅን ፡ የሚሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ አጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡፡

፱ ፤ ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

መዝሙር ፡ ፻፩ ።

ጸሎት ፡ ባሕታዊ ፡ ሶበ ፡ ይቴክዝ ፡ ወይክዑ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስእለቶ ።

ጸሎተ ባሕታዊ ፡ ዘጸለየ ፡ ባሕታዊ ፡ ይላል ፤ ትሩፍ ፡ አንድም ፡ ማናቸውም ፡ ባሕታዊ ፡ ባዘነ ፡ በተከዘ ፡ ጊዜ ፡ ልመናውንም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የጸለየው ፡ ጸሎት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አንድም ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ወጸለየ ፡ ጦቢት ፡ ጸሎተ ፡ ትፍሥሕት ፡ ጸሎት ፡ ብሂል ፡ ተናገሮ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲል ።

፪ ፤ ስምዓኒ ፡ እግዚኦ ፡ ጸሎትየ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ አቤቱ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ወይብጻሕ ፡ ቅድሜከ ፡ ገዓርየ ።

ጩኸቴም ፡ ከፊትህ ፡ ይድረስ ።

፫ ፤ ወኢትሚጥ ፡ ገጸከ ፡ እምኔየ ።

ገጸ ፡ ምሕረትህን ፡ ገጸ ፡ ረድኤትህን ፡ ከኔ ፡ ወደዚያ ፡ አትመልሰው ።

በዕለተ ፡ ምንዳቤየ ፡ አፅምእ ፡ ዕዝነከ ፡ ኀበ ፡ የ ።

በመከራዬ ፡ ቀን ፡ ዕዝነ ፡ ፈቃድህን ፡ ወደኔ ፡ መልሰህ ፡ ስማኝ ፤ ስማኝ ፡ እንጂ ፡ ኢትሚጥ ።

እመ ፡ ዕለተ ፡ እጼውዓከ ፡ ፍጡነ ፡ ስምዐኒ ። መገ ፡ ፻፴፯ ፡ ፫ ።

በለመንኩህ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥነህ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

፬ ፤ እስመ ፡ ኀልቀ ፡ ከመ ፡ ጢስ ፡ መዋዕልየ ።

ዘመኔ ፡ እንደ ፡ ጢስ ፡ ማለት ፡ ጢስ ፡ በንኖ ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ ዘመኔም ፡ በመከራው ፡ ተፈጽምዋልና ።

ወንቅጸ ፡ ከመ ፡ ማዕር ፡ አዕፅምትየ ።

ሰውነቴም ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ ደርቋልና ።

፭ ፤ ተቀሠፍኩ ፡ ወየብሰ ፡ ከመ ፡ ሣዕር ፡ ልብየ ።

ሰባ ፡ ዘመን ፡ በሠውጠ ፡ መከራ ፡ የተገረፍሁ ፡ ሆንሁ ፡ ልቡናዬም ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ ደረቀ ፡ ማለት ፡ አእምሮዬ ፡ ተለየኝ ።

እስመ ፡ ተረሥዐኒ ፡ በሊዐ ፡ እክል ።

ብተው ፡ ብተው ፡ እህል ፡ መብላት፡ ተዘንግቶኛልና ፡ አግኝቶ ፡ አይደለም ፡ ማጣቱን ፡ መናገር ፡ ነው ።

፭ ፡ እምቃለ ፡ ገዓርየ ፡ ጠግዓ ፡ ሥጋየ ፡ ዲበ ፡ አዕፅምትየ ።

ከመከራዬ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሰውነቴ ፡ ደረቀ ፡ አንድም ፡ ሥጋዬ ፡ ካጥንቴ፡ ጋራ፡ ተጣጋ ። ኢዮ ፡ ፲፱፡ ፳

፮ ፡ ወኮንኩ ፡ ከመ ፡ አድግ ፡ መረብ ፡ ዘገዳም ። ኤር ፡ ፲፪፡ ፳፬ ።

በበረኃ ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ በዳ ፡ አህያ ፡ ሆንሁ ፡ ይህ ፡ የበዳ ፡ አህያ ፡ ቆርበተ ፡ ስስ ፡ ነው ፡ አራዊት ፡ ሁሉ ፡ ይጣሉታል ፡ ቀን ፡ ከቦታው፡ አይወጣም ፡ ሌሊት ፡ ከተራራ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ነፋስ፡ መልሶ ፡ አፉን ፡ ከፍት ፡ ክድን ፡ ከፍት ፡ ክድን ፡ ያደርገዋል ፡ ሐለስትዮታት ፡ ይቀውሙ ፡ ማዕከለ ፡ አድባር ፡ ወያበቅዉ ፡ አንፎሙ ፡ መንገለ ፡ ነፋስ ፡ እንዲል ።

መልእኩ ፡ የማር ፡ የወሀ መዓዛ ፡ አምጥቶ ፡ ያሸተዋል ፡ የሦስት ፡ ቀን፡ መንገድ፡ ሂዶ፡ ሣሩን፡ በልቶ ፡ ወሀውን ፡ ጠጥቶ ፡ ተሐዋስያን ፡ ከቦታቸው ፡ ሳይወጡ ፡ ዕለቱን ፡ ከቦታው ፡ ገብቶ ፡ ያድራል ።

ወኮንኩ ፡ ከመ፡ጉጓ፡ውስተ ፡ ቤት፡ሌሊት

ውስተ ፡ ቤት ፡ ሌሊተ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሌሊት ፡ ይላል ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ እንዳለች ፡ ቁንጫ ፡ ሆንሁ ፡ እሷ ፡ አትተኛ ፡ ሰውን ፡ አታስተኛ ፡ በመከራ ፡ ታሳድራለች ፤ አንድም ፡ ከመ ፡ ጋጋኖ ፡ ይላል ፡ እንደ ፡ ጋጋኖ ፡ ሆንሁ ፡ ያ ፡ እየጮኸ ፡ እንዲያድር ፡ ባለመከራ፡ ሆንሁ ፡ አንድም ፡ ከመ ፡ ጉጓ ፡ እንደ ፡ ጉጉት ፡ ሆንሁ ፡ ቀን ፡ ቀን ፡ አትወጣም ፡ ከያፈ ፡ ንስር ፡ እስከ ፡ ያፈ ፡ ድንቢጥ ፡ ያሉ ፡ አእዋፍ ፡ ሁሉ ፡ ይሠለጥኑበታል ፡ እንዲህ ፡ ሆንሁ ፡ አንድም ፡ ቤቷን ፡ በሰገነት ፡ እንደምትሠራ፡ ያፍ ፡ ሆንሁ ፡ ቀን ፡ ስትሠራ ፡ ውላ ፡ ማታ ፡ ይጠፋታል ፡ አንድም ፡ ይፈርስባታል ፡ የት ፡ ውዬ ፡ የት ፡ ልደር ፡ እያለች ፡ እንድትኖር ።

፯ ፡ ተጋሕኩ ፡ ወኮንኩ ፡ ከመ ፡ ዖፍ ፡ ባሕታዊ ፡ ውስተ ፡ ናኅስ ።

ሰባ ፡ ዘመን ፡ ለመከራው ፡ የተጋሁ፡ በሰገነት ፡ እንደምትኖር ፡ ወፍም ፡ ሆንሁ ፡ የጭቃ ፡ ቤት ፡ ሠርታ ፡ የምትኖር ፡ ወፍ ፡ አለችና ፡ አንድም ፡ እንደ ፡ ጉጉት ፡ ሆንሁ ።

፰ ፡ ወነሶሙ ፡ አሚረ ፡ ይጼዕሉኒ ፡ ጸላእትየ

ጠላቶቼ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይሰድቡኛል ።

ወእለኒ ፡ ይሰዱኒ ፡ ይሰክተዩ ፡ ላዕሌየ ።

ይሰዱኒ ፡ ከሀገሬ ፡ አስወጥተው ፡ የሚሰዱኝ ፡ (ይወስዱኒ) ፡ ማርከ

ው ፡ የሚወስዱኝ ፡ በኔ ፡ ይማማሉ ብኛል ፡ ሴራ ፡ ይቆርጡብኛል ፡ ወዳንተ ፡ የመጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስረህ ፡ ስደድልኝ ፡ ወደኔ ፡ የመ ጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስሬ ፡ እሰድድ ልሃለሁ እየተባባሉ ።

፱ ፤ እስመ ፡ ሐመደ ፡ ከመ ፡ እክል ፡ ቀማሕኩ

አመዱን ፡ እንደ ፡ እህል ፡ ተመገ ብሁት ፡ ማለት ፡ ተዋርዷቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ አንድም ፡ ግዳይ ፡ ብለው ፡ ይጥሏቸዋል ፡ ሲነሱ ፡ አመዱን ፡ በግንባራቸው ፡ በከንፈ ራቸው ፡ ይዘውት ፡ ይነሣሉና ፡ አን ድም ፡ አሽር ፡ ባሸሩን ፡ ጓያውን ፡ ባቄላውን ፡ ይሰጧቸዋልና ፡

ወስቴየኒ ፡ ምስለ ፡ አንብዕየ ፡ ሰተይኩ ።

መጠጤንም ፡ ከዕንባ ፡ ጋራ ፡ ጠ ጣሁ ፡ ኢሳ ፡ ፴ ፡ ፳ ።

፲ ፤ እምገጸ ፡ መቅሠፍት ፡ መዓትከ ።

ይህም ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ያገኘኝ ፡ ገጸ ፡ መዓትህ ፡ ከመገለጽ ፡ የተነ ሣ ፡ ነው ።

እስመ ፡ አንሣእከኒ ፡ ወነፃሕከኒ ።

አንስተህ ፡ ጥለኸኛልና ፡ አንሥተ ው ፡ የጣሉት ፡ እንዲጎዳ ፡ ጎድተኸ ኛልና ፡ አንድም ፡ አክብረህ ፡ አዋ ርደኸኛልና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አድ ርገህ ፡ ቋሚ ፡ ለጓሚ ፡ አድርገ ኸኛልና ፡ ገብሮ ፡ ገዶ ፡ ዓመቶ ፡

ወለቶ ፡ ተብዬ ፡ እንድሰደብ ፡ አድ ርገኸኛልና ።

፲፩ ፤ ወመዋዕልየኒ ፡ ከመ ፡ ጽላሎት ፡ ኀለፈ

ዘመኔም ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ተፈጸመ ።

ወአንሂ ፡ ከመ ፡ ሣዕር ፡ የበስኩ ።

እኔም ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ ደረቅሁ ፡ ማ ለት ፡ ወዝ ፡ ልምላሜ ፡ እንዳይገኝ በት ፡ አእምሮ ፡ ተለየኝ ።

፲፪ ፤ አንተሰ ፡ እግዚኦ ፡ ለዓለም ፡ ትነብር

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ለዘላለም ፡ ትኖራለኅ ።

ወዝክርከኒ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ።

ስም ፡ አጠራርህም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ይኖራል ፡ ሰቆ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ።

፲፫ ፤ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ ወተሣሃላ ፡ ለጽዮን ።

አቤቱ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነ ሥተህ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ይቅር ፡ በላት ፡ ማለት ፡ አገሪቱ ፡ እንድት ቀና ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንድትሠራ ፡ አድርግ ።

እስመ ፡ ጊዜሃ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ትሣሃላ ።

ይቅር ፡ ትላት ፡ ዘንድ ፡ ጊዜዋ ፡ ደር ሷልና ።

ወበጽሐ ፡ ዕድሜሃ ።

የይቅርታዋም ፡ ዘመን ፡ ደርሷልና ።

፲፬ ፤ እስመ ፡ ሠምሩ ፡ አግብርቲከ ፡ ዕበኒሃ

ባሮችህ ፡ ትሩፋን ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ደንጊያዋን ፡ ወድደዋልና ።

ወእከበርዎ ፡ ለመሬታ ።
መሬቷንም ፡ ወደዋልና ፡ ጨው ፡
ከብሮ ፡ ዋለ ፡ እንዲሉ ፡ አንድም ፡
የናፍቆት ፡ ደንግያዋን ፡ ተንተርሰ
ነው ፡ መሬቷን ፡ ልሰነው ፡ ስላሉ ፡
የባቢሎን ፡ ደንግያዋ ፡ ሻፎ ፡ መ
ሬቷ ፡ ቀይ ፡ ነው ፡ የኢየሩሳሌም ፡
ግን ፡ ደንግያዋ ፡ መዓዝን ፡ መሬቷ ፡
መረሬ ፡ ነውና ፡ አንድም ፡ (ዕበኒሃ)፡
ኢታምልክን፡ (መሬታ) ፡ ዘጠኙን ፡
ሕገጋት ፡ አንድም ፡ (ዕበኒሃ) ፡ ዐሠ
ርቱ ፡ ቃላትን ፡ (መሬታ) ፡ ወነበቦ ፡
ወነበቦ ፡ ያለውንም ፡ ቃል ፡ ጠበቅ
ን ፡ ብለዋልና ።

አንድም ፡ (እስመ ፡ ሠምሩ)፡ባሮችህ፡
እለ ፡ ንዕማን ፡ የወልደ ፡ አዴር ፡
ቢቶደድ ፡ ነው ፡ ከሰልፍ ፡ ላይ ፡
ሲዋጋ ፡ ተመትቶ ፡ በደም ፡ አማ
ቂት ፡ አካሉ ፡ በለምፅ ፡ ነዶ ፡ ይኖር፡
ነበር ፡ ሚስቱ ፡ ሲወጣ ፡ ሲገባ ፡ አካ
ሉን ፡ እያየች ፡ ስታዝን ፡ ትኖር ፡
ነበር ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ የም
ትሆን ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ማርኮ ፡
ወስዶ ፡ ደንገጥር ፡ ትሁንሽ ፡ ብሎ ፡
ለሚስቱ ፡ ሰጥቷት ፡ ነበርና ፡ ምን
ው ፡ ታዝኛለሽ ፡ አለቻት ፡ ምነው ፡
አላዝን ፡ የባለቤቴ ፡ አካሉ ፡ በለም
ፅ ፡ ነዶ ፡ አለቻት ፡ መፍትው ፡
ይሑር፡ ኀበ ፡ ነቢየ ፡ እግዚአብሔር ፡
ከኔ ፡ አገር ፡ ቢሄድ ፡ ነቢየ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ያድነው ፡ ነበር ፡ አለቻ
ት ፡ ከጌታው ፡ ቤት ፡ ውሎ ፡ ማታ ፡
ሲገባ ፡ ይህን ፡ ነገረችው ፡ እሱም ፡
ለጌታው ፡ ነገረው ፡ ብዙ ፡ ወርቅ ፡
ብር ፡ በሁለት ፡ በቅሎ ፡ አስጭኖ ፡
አፈውሶ ፡ ለንዕማን ፡ ቍልኤየ ፡
ብሎ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰደደ ፡
ርዕዩ፡ ዘከመ ፡ የኃሥሥ፡ ምክንያተ ፡
ወልደ ፡ አዴር ፡ ይላል ።

ፀብ ፡ የሻ ፡ ዳኛ ፡ አምጡ ፡ ይላል ፡
የዶሮ ፡ ሻኛ ፡ እንዲሉ ፡ በምን ፡ ም
ክንያት ፡ ልጣለው ፡ ሲል ፡ አያች
ሁን ፡ ቦኑ ፡ አነ ፡ እክል ፡ ቀቲለ ፡
ወአሕይዎ ፡ እኔ ፡ ማዳን ፡ መግደል፡
የሚቻለኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡
በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ልጣ
ላው ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እለ ፡
ካጠገቡ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡
ማድረግ ፡ የሚቻለው ፡ ነቢየ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ በሀገርህ ፡ እንዳለ ፡ ታ
ውቅ ፡ የለምን ፡ ወደዚያ ፡ አትሰደ
ውምን ፡ አሉት ፤ አንድም ፡ እሱ ፡
ራሱ ፡ (ኤልሣዕ) ፡ ከዚያው ፡ ነበ
ርና ፡ እራሱን ፡ አርቆ ፡ እንዲህ ፡
ይለዋል ፡ አንድም ፡ ከዚያ ፡ ሳይ
ኖር ፡ በፀጋ ፡ ዐውቆ ፡ የመጣ ፡ ወ
ደኔ ፡ ነውና ፡ ወደኔ ፡ ላከው ፡ አለው፡
እሱም ፡ (ኤልሣዕም) ፡ እስራኤል ፡
ለምፅ ፡ ይጸየፋሉና ፡ በዚያው ፡ ዮር
ዳኖስ ፡ ሄደህ ፡ ተጠመቅ ፡ ብሎ ፡
ይልክበታል ፡ እኔ ፡ ነቢየ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ቢሉ ፡ ባይኑ ፡ አይቶ ፡ በ

ቃሉ ፡ ተናግሮ ፡ በእጁ ፡ ዳስሦ ፡ ያድ
ነኛል ፡ ብዬ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ የወሀ ፡
የወሀ ፡ ምናለኝ ፡ ቀሐ ፡ እንዲሉ ፡ የ
ወሀ ፡ የወሀማ ፡ ምንተ ፡ ይቤሉኒ ፡
ማያተ ፡ ብሔርየ ፡ ባብና ፡ ወፋርፋ ፡
ኢይሄይሱኑ ፡ ማያተ ፡ ብሔርየ ፡
እማያተ ፡ ብሔሮሙ ፡ ለእስራኤል ፡
ከዚህ ፡ ከቀዝቃዛ ፡ ከደጋ ፡ ወሀማ ፡
ሙቀት ፡ ያለው ፡ ያገሬ ፡ ወሀ ፡ አይ
ሻልምን ፡ ብሎ ፡ ተቈጥቶ ፡ ተመለ
ሰ ፡ ከኤልሣዕ ፡ ዘንድ ፡ ተልከው ፡
የመጡ ፡ ሰዎች ፡ ግድ ፡ የለህም ፡
ነቢየ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተናገ
ረው ፡ ነገር ፡ አይቀርም ፡ ሂደህ ፡
ተጠመቅ ፡ ብለውት ፡ አንድም ፡
የሱው ፡ አሽከሮች ፡ ለኛም ፡ ለፀብ ፡
ይመቸናል ፡ ሂደህ ፡ ተጠመቅ ፡ ብለ
ውት ፡ ነው ፡ ወርዶ ፡ ሶስት ፡ ጊዜ ፡
ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ ብሎ ፡ቢጠመቅ ፡
ከለምጹ ፡ ነጽቷል ። ከዚያ ፡ ተመ
ልሶ ፡ ሂዶ ፡ ወርቁን ፡ ብሩን ፡ ከፊ
ቱ ፡ አፍስሶለታል ፡ እሣየጦኑ ፡ ለ
ፀጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፀጋ ፡ እግዚ
አብሔርን ፡ ለወርቅ ፡ እሸጠዋለ
ሁን ፡ ብሎ ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ
ታል ፡ እንኪያ ፡ ምን ፡ ላድርግልህ ፡
አለው ፡ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡
እመን ፡ አለው ፡ ይህማ ፡ እንዳይ
ሆን ፡ ጌታዬ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡
ሲሄድ ፡ እኔን ፡ አስከትሎ ፡ ነው ፡
ለጣዖት ፡ ሲሰግድ ፡ ቅሉ ፡ የኔን ፡
ትከሻ ፡ ይዞ ፡ ነው ፡ እንደምን ፡
አድርጎ ፡ ይሆንልኛል ፡ አለው ፡
ይህንማ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ዐውቃለሁ ፡
አለው ፡ እንዲህስ ፡ ባደርግ ፡ አለው ፡
እንዴት ፡ አለው ፡ ከኢየሩሳሌም ፡
አፈር ፡ ደንጊያ ፡ ጭኜ ፡ ሂጄ ፡ ከ
ቤተ ፡ ጣዖት ፡ አጠገብ ፡ መደብ ፡
አሠርቼ ፡ እሱ ፡ ለጣዖት ፡ ሲሰግድ ፡
እኔ ፡ ለመሬቱ ፡ ብሰግድስ ፡ አለው ፡
መልካም ፡ ነው ፡ አለው ፡ ወሐረ ፡
በኪዳነ ፡ ምድር ፡ ይላል ፡ መሬቱ
ን ፡ በሁለት ፡ በቅሎ ፡ አስጭኖ ፡
ሂዶ ፡ ጌታው ፡ ለጣዖት ፡ ሲሰግድ ፡
እሱ ፡ ለመሬቱ ፡ የሚሰግድ ፡ ሁ
ኗል ፡ ይኸውም ፡ ሃይማኖት ፡ ሁ
ኖት ፡ ተጠቅሞበታልና ፡ እንዲህ ፡
አለ ። ፬ ፡ ነገ ፡ ፳ ፡ ፩-፲፱ ።

፲፭ ፡ ወይፍርሁ፡አሕዛብ ፡ ስመከ፡እግዚኦ

አቤቱ ፡ ሠራዊቱ ፡ ያምላክነትህን ፡
ስም ፡ ይፍሩ ፡ ማለት ፡ ፈርተው ፡
ያምልኩ ።

ወኵሎሙ ፡ ነገሥት ፡ ለስብሐቲከ ።

ነገሥታቱም ፡ ሁሉ ፡ ለጌትነ
ትህ ፡ ይገዙ ፤ አንድም ፡ (ወይፍር
ሁ ፡ አሕዛብ) ፡ ቂሮስ ፡ ዳርዮስ ፡
ስምህን ፡ ፈርተው ፡ ያመስግኑ ፡
(ወኵሎሙ ፡ ነገሥት ፡ ዮሴዕ ፡ ዘሩ
ባቤልም ፡ ለጌትነትህ ፡ ይገዛሉ ፡
ይገዙ ።

፲፮ ፤ እስመ ፡ የሐንፃ ፡ እግዚአብሔር ፡
ለጽዮን ።

እግዚአብሔር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡
እንድትሠራ ፡ ያደርጋልና ።

ወኢተቈጥዐ ፡ ስእለቶሙ ። መዝ ፡ ፳፩፡፳፬

በጌትነቱም ፡ ይገለጻልና ።

፲፯ ፡ ወነጸረ ፡ ላዕለ ፡ ጸሎተ ፡ ነዳይ ።

ትሩፍ ፡ ያቀረበውን ፡ ልመናም ፡ ተቀብሏልና ፤ ወነጸረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕለ ፡ አቤል ፡ ወላዕለ ፡ መሥዋዕቱ ፡ እንዲል ።

ወኢተቈጥዐ ፡ ስእለቶሙ ። መዝ ፡ ፳፩፡፳፬

የትሩፋንን ፡ ልመናቸውን ፡ ቸል ፡ አላለም ፡ አላነጠበምና ።

፲፰ ፡ ወትጽሐፍ ፡ ዛቲ ፡ ለካልእ ፡ ትውልድ ።

ይህቺ ፡ ዕለተ ፡ ሚጠት ፡ ለሌላ ፡ ትውልድ ፡ ተሰጠች ፤ ማለት ፡ በእስራኤል ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ በኢኮንያን ፡ ተማርከዋል ፡ በሰላትያል ፡ ተገዝተዋል ፡ በዘሩባቤል ፡ ወጥተዋል ። በአሕዛብ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ በስልምናሶር ፡ ተማርከዋል ፡ በዮልማሮዴቅ ፡ ተገዝተዋል ፡ በብልጣሶር ፡ ወጥተዋልና ። አንድም ፡ በካልዕ ፡ ትውልድ ፡ በሌላ ፡ ትውልድ ፡ ተደረገች ፡ ማለት ፡ በቂሮስ ፡ በዳርዮስ ፡ አንድም ፡ አበው ፡ አልቀው ፡ ውሉድ ፡ ወጥተዋልና ፡ ለካልዕ ፡ ትውልድ ፡ አለ ።

ሕዝብ ፡ ዘይትፈጠር ፡ ይሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ሁለተኛ ፡ የሚነሣ ፡ ሕዝብ ፡ ከጊዜው ፡ ደርሶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግነዋል ። መዝ ፡ ፳፩ ፡ ፳፩ ። ኢሳ ፡ ፵፫ ፡ ፳፩ ።

፲፱ ፡ እስመ ፡ ሐወጸ ፡ እምሰማይ ፡ መቅደሶ

እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ ሁኖ ፡ መመስገኛው ፡ የምትሆን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ በረድኤት ፡ ጎበኝቷልና ።

እግዚአብሔር ፡ ሐወጸ ፡ እምሰማይ ፡ ዲበ ምድር ።

ዲበ ፡ ምድር፡ ለማለት፡ደግሞታል፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ ሁኖ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለከተ ።

፳ ፡ ከመ ፡ ይስማዕ ፡ ገዓሮሙ ፡ ለሙቁሓን

የትሩፋንን፡ ልመና፡ ይሰማ፡ ዘንድ ።

ወከመ ፡ ያሕይዎሙ ፡ ለደቂቀ ፡ ቅቱላን

ኢሳ ፡ ፶፩ ፡ ፲፬ ።

የሙታንን ፡ ልጆች ፡ ትሩፋንንም ፡ ከመከራው ፡ ያድናቸው ፡ ዘንድ ፡

፳፩ ፡ ከመ ፡ ይንግሩ ፡ በጽዮን ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ። ወስብሐቲሁኒ ፡ በኢየሩሳሌም

ከመ ፡ ይንግሩ ፡ በጽዮን ፡ ወበኢየሩሳሌም ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወስብሐቲሁኒ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ (በጽዮን) ፡ በከተማ ፡ ይነግሩ ፡ ዘንድ ፡ ጌትነቱንም ፡ (በኢየሩሳሌም) ፡ በገጸር ፡ ይነግሩ ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ።

፳፪ ፡ ሶበ ፡ ተጋብኡ ፡ አሕዛብ ፡ ኅቡረ ።

ሠራዊቱ ፡ በሃይማኖት ፡ ባንድነት ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡

መንግሥትኒ ፡ ከመ ፡ ይትቀነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ነገሥታቱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ አንድም ፡ ቂሮስ ፡ ዳርዮስ ፡ በሃይማኖት ፡ አንድነት ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ (ወነገሥትኒ) ፡ ዮሴዕ፡ዘሩባቤልም፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ።

፳፫ ፤ ወተሰጥዎ ፡ በፍኖተ ፡ ኃይሉ ።

ኃይልን ፡ አድርጎ ፡ ባስማረካቸው ፡ ጎዳና ፡ አወጣቸው ፤ አንድም ፡ በየ ጎዳናው ፡ ኃይልን ፡ አድርጎ ፡ ማለት ፡ በተአምራት ፡ አወጣቸው ።

ንግረኒ ፡ ውኅዶን ፡ ለመዋዕልየ ።

በባቢሎን ፡ የምኖረውን ፡ የዘመኔን ፡ ልክ ፡ ንገረኝ ።

፳፬ ፤ ኢትስደኒ ፡ በመንፈቀ ፡ ዓመትየ ።

ሰባ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ቢለው ፡ እንኪያስ ፡ ይህ ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ሳይፈጸም ፡ በመከራው ፡ አታጥፋኝ ፤ አንድም ፡ ለሁሉ ፡ አድርጎ ፡ ተናግሮታል ፡ ብለህ ፡ (ንገረኒ) ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የምኖረውን ፡ የዘመኔን ፡ ልክ ፡ ንገረኝ ፡ ሰባ ፡ ሰማንያም ፡ እንደሆነ ፡ ወእመ ፡ ፈጠሮ፡ ይእተ ፡ አሚረ ፡ ይኤዝዞ ፡ እንዴል ፤ ሲፈጥረው ፡ የዘመኑን ፡ ልክ ፡ አውቆ ፡ ነውና ፡ የሚፈጥረው ። (ኢትስደኒ) ፡ ይህ ፡ አንተ ፡ የሰጠኸኝ ፡ ዘመን ፡ ሳይፈጸም ፡ በእኩሌታው ፡ አታጥፋኝ ።

ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ ዓመቲከ ።

ዘመንህ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ አይፈጸምምና ።

፳፭ ፤ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ አቅደምከ ፡ ሣረርካ ፡ ለምድር ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ምድርን ፡ አስቀድመህ ፡ ፈጠርህ ፡ (ሐተታ) ፡ አቅደምከ ፡ አለ ፡ ከማን ፡ ቢሉ ፡ ከሰማይ ፡ ምነው ፡ የሰማይና ፡ የምድርማ ፡ ተፈጥሯቸው ፡ በቀዳሚ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አይደለምን ፡ ቢሉ ፡ በመታየት ፡ አቅደምከ ፡ አለ ፡ ዛሬ ፡ ቅሉ ፡ ሰማይ ፡ አይታይምና ። አንድም ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ለምድር ፡ ሰጥተህ ፡ ከመታየቷ ፡ መፈጠሯን ፡ ብቻ ፡ አስቀደምህ ፡ ከዚህ ፡ እስከ፡ ብሩህ ፡ ሰማይ ፡ ወህ ፡ መልቶ ፡ ነበርና ።

ወግብረ ፡ እደዊከ ፡ እማንቱ ፡ ሰማያት ።

ሰማያትም ፡ የእጅህ ፡ የቃልህ ፡ ፍጥረት ፡ ናቸው ። ዕብ ፡ ፩ ፡ ፲ ።

፳፮ ፤ እማንቱሰ ፡ ይትኀጐሉ ፡ ወአንተሰ ፡ ትሄሉ ።

ሰማይ ፡ ምድር ፡ ያልፋሉ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ አታልፍም ።

ወኵሉ ፡ ከመ ፡ ልብስ ፡ ይበሊ ።

ሁሉ ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ያልቃል ፤ ዕድሜና ፡ ጨርቅ ፡ ሲበጣጠስ ፡

ያልቃል ፡ እንዲሉ ፡ ለሁሉ ፡ ውራጅ ፡ አለው ፡ ለልብስ ፡ ግን ፡ ውራጅ ፡ የለውምና ። ኢዮ ፡ ፬ ፡ ፲፱ ። ኢሳ ፡ ፴፬ ፡ ፬ ።

ወከመ ፡ ሞጣሕት ፡ ትዌልጦሙ ፡ ወይትዌለጡ ።

እንደ ፡ ሌታ ፡ ቀን ፡ ግምጃ ፡ ትለዋውጣቸዋለህ ፡ ይለዋወጣሉ ፡ ማለት ፡ በሕፃንነት ፡ በእርጅና ፡ በሕይወት ፡ በሞት ፡ በሰብአ ፡ ትካት ፡ በሰብአ ፡ ሰዶም ፡ በሰብአ ፡ ገሞራ ፡ ትለዋውጣቸዋለህ ፡ ይለዋወጣሉ ።

እንድም ፡ (አንተ ፡ እግዚኦ) ፡ ሥጋን ፡ ከነፍስ ፡ አስቀድመህ ፡ ፈጠርህ ፡ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአርያነ ፡ ወበአምሳሊነ ፡ እንዲል ፡ (ሐተታ) ፡ ተፈጥሯቸው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አይደለምን ፡ ቢሉ ፡ የነፍስ ፡ ተፈጥሮ ፡ እምኀበ ፡ አልቦ ፡ ነው ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተመቸ ፡ ምንም ፡ ሥጋ ፡ የተገኘ ፡ (የተፈጠረ) ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ ቢሆን ፡ የሥጋ ፡ ምክንያት ፡ የሚሆኑ ፡ አራቱ ፡ ባሕርያት ፡ የተፈጠሩ ፡ እሑድ ፡ ነውና ፡ ግብር ፡ እምግብር ፡ ነው ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ለነገር ፡ ከነገር ፡ አካል ፡ ይቀድማልና ፡ (ወግብረ ፡ እደዊከ) ፡ ነፍሳት ፡ የእጅህ ፡ የቃልህ ፡ ፍጥረት ፡ ናቸው ፡ (እማንቱሰ) ፡ ነፍሳት ፡ ይጠፋሉ ፡ አባ ፡ ለቅዱን ፡ እንዳስጠኙት ፡ ነፍስ ፡ በነፍስስ ፡ ጥፋት ፡ የለባትም ፡ ብሎ ፡ ከኀሣርም ፡ ከክብርም ፡ አልደረሰችም ፡ ይህስ ፡ መቼ ፡ ይሆናል ፡ ከኃሣር ፡ ከወጡ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መግባት ፡ ከክብርም ፡ ከወጡ ፡ ገሃነም ፡ መውረድ ፡ ነው ፡ ሦስት ፡ ቦታ ፡ የለ ፡ ወኢዘከረ ፡ መጽሐፍ ፡ አምላካዊ ፡ ፫ተ ፡ መካናተ ፡ ይላል ፡ ብሎ ፡ በኃጢአት ፡ መለወጧን ፡ ሲያይ ፡ አንድም ፡ መለያየት ፡ የጋራ ፡ ከሆነ ፡ ብሎ ፡ (ወአንተሰ ፡ ትሄሉ) ፡ አንተ ፡ ግን ፡ አታልፍም ፡ (ወኵሉ) ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ያልፋል ፡ ወከመ ፡ ሞጣሕት ፡ ትጠውሞሙ ፡ ወይጠወሙ ፡ ይላል ፡ እንደ ፡ ሻግሌ ፡ ግምጃ ፡ መጋረጃ ፡ ትጠቀልላቸዋለህ ፡ ይጠቀለላሉ ፡ ያን ፡ አንዱን ፡ ከሁለት ፡ ሁለቱን ፡ ካራት ፡ አራቱን ፡ ከስምንት ፡ አጥፈው ፡ በሣጥን ፡ ያኖሩታል ፡ እሱም ፡ ሰዓቱን ፡ በዕለት ፡ ዕለቱን ፡ በወር ፡ ወሩን ፡ ባመት ፡ ዓመቱን ፡ በሺህ ፡ ሺሁን ፡ በሁለት ፡ ሺህ ፡ ሁለቱን ፡ ሺህ ፡ ባራት ፡ ሺህ ፡ አራቱን ፡ ሺህ ፡ በስምንት ፡ ሺህ ፡ አጥፎ ፡ በኀልፈት ፡ ሣጥን ፡ ይከትተዋልና ። ኢሳ ፡ ፶ ፡ ፱ ። ዳን ፡ ፬ ፡ ፴፬ ። ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፳፯ ።

፳፮ ፡ ወአንተሰ ፡ አንተ ፡ ክመ ። ዳን ፡ ፯ ፡ ፲፬ ።

አንተ ፡ ግን ፡ መቼም ፡ መች ፡ አንተ ፡ ነህ ።

ወዓመቲከኒ ፡ ዘኢየኃልቅ ።
ዘመንህም ፡ አይፈጸምም ።
፳፰ ፤ ደቂቀ ፡ አግብርቲከ ፡ ይነብርዋ ።
ተንሥእ ፡ እግዚእ ፡ ወተሠሃላ ፡ ለጽዮን ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ቍ ፡ ፲፫ ። የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ወርሰዋት ፡ ይኖራሉ ።
ወዘርዖሙኒ ፡ ለዓለም ፡ ይጸንዕ ።
ልጆቻቸውም ፡ ለዘላለም ፡ ጸንተው ፡ ወርሰዋት ፡ ይኖራሉ ፤ ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ከሚጠት ፡ በኋላ ፡ ደቂቀ ፡ እስሙናይን ፡ ወርሰዋት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ ኢሳ ፡ ፶፩ ፡ ፮ ። ዕብ ፡ ፩ ፡ ፲-፲፪ ። ራእ ፡ ፳ ፡ ፲፩ ።

መዝሙር ፡ ፻፪ ።

፩ ፤ ትባርኮ ፡ ነፍስየ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ቍ ፡ ፳፪ ፡ መዝ ፡ ፻፫ ፡ ፩ ፡ ፴፭ ።
ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ ሰውነቴ ፡ አንድም ፡ ልቡናዬ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታመሰግነዋለች ።
ወኵሉ ፡ አዕፅምትየ ፡ ለስሙ ፡ ቅዱስ ።
ስሞ ፡ ቅዱሰም ፡ ይላል ፡ ሕዋሳቴ ፡ ሁሉ ፡ ፅኑዕ ፡ ከሀሊ ፡ የሚሆን ፡ ስሙን ፡ ያመሰግናሉ ፤ አንድም ፡ ለስሙ ፡ ቅዱስ ፡ ብለህ ፡ ፅኑዕ ፡ ከሀሊ ፡ ለሚሆን ፡ ስሙ ፡ ምስጋና ፡ ያቀርባሉ ።
፪ ፤ ትባርኮ ፡ ነፍስየ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ደገመው ።
ወኢትርሣዕ ፡ ኵሎ ፡ ሰብሓቲሁ ።
ትሩፍ ፡ ትባርኮ ፡ ነፍስየ ፡ አልኸ ፡ አበጀህ ፡ ጌትነቱን ፡ ሁሉ ፡ አትርሣ ፡ አትዘንጋ ።
፫ ፤ ዘይሠሪ ፡ ለከ ፡ ኵሎ ፡ ኃጢአተከ ።
ኃጢአትህን ፡ ሁሉ ፡ የሚያስተሠርይልህ ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፡ ኃጢአትህን ፡ ሁሉ ፡ የሚያስተሠርይልህ ፡ ጌትነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አትርሣ ።
ዘይፌውሰከ ፡ እምኵሉ ፡ ደዌከ ።
ከደዌህ ፡ ሁሉ ፡ የሚያድንህ ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፡ የሚያድንህ ፡ ጌትነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አትርሣ ።
፬ ፤ ዘያድኅና ፡ እሙስና ፡ ለሕይወትከ ።
ሰውነትህን ፡ ከጥፋት ፡ የሚያድናት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፡ የሚያድናት ፡ ጌትነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አትርሣ ።
ዘይኬልለከ ፡ በሣህሉ ፡ ወበምሕረቱ ።
በይቅርታው ፡ በቸርነቱ ፡ ከመከራው ፡ ሁሉ ፡ የሚሠውርህ ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፤ የሚሠውርህ ፡ ጌትነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አትርሣ ።
፭ ፤ ዘያጸግባ ፡ እምበረከቱ ፡ ለፍትወትከ
ሰውነትህን ፡ ከበረከቱ ፡ ሰጥቶ ፡

ዶ.ስ ፡ የሚያሰኛት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፡ ዶ.ስ ፡ የሚያሰኛት ፡ ጌትነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አትርሣ ። ፴፩ ፡ ፩ ።

ዘይሔድሳ ፡ ከመ ፡ ንስር ፡ ለውርዙትከ ።

ሰውነትህን ፡ እንደ ፡ ዖፌ ፡ ፊንክስ ፡ የሚያድሳት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፡ የሚያድሳት ፡ ጌትነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አትርሣ ። (ታሪክ) ፡ ዖፌ ፡ ፊንክስ ፡ ብልየት ፡ ያገኘው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከቈላ ፡ ወርዶ ፡ ከሁለት ፡ ከሶስት ፡ ላይ ፡ ዕንጨት ፡ ይሰበስባል ፡ አንድም ፡ ባለወጎች ፡ ይሰበስቡለታል ፡ ተራራ ፡ ተራራ ፡ ያህል ፡ ሲሆን ፡ ከውቅያኖስ ፡ አብዶ ፡ የሚባል ፡ ድኝ ነት ፡ ያለው ፡ ጭቃ ፡ አለ ፡ ከዚያ ፡ ሂዶ ፡ ተቀብቶ ፡ መጥቶ ፡ ከተቆለለው ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ ሁለት ፡ ክንፉን ፡ ያማታዋል ፡ ወይወጽእ ፡ እሳት ፡ እማዕከለ ፡ ክነፊሁ ፡ ይላል ፡ እሳት ፡ ከክንፉ ፡ ወጥቶ ፡ ያቃጥለዋል ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ዝናም ፡ አይዘንምም ፡ ባምስት ፡ መቶ ፡ ባምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ለተሐድሶተ ፡ ንስር ፡ ካፊያ ፡ ያካፋል ፡ በነጋው ፡ ትል ፡ ያህል ፡ ሁኖ ፡ ተፈጥሮ ፡ ያድራል ፡ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ዖፌ ፡ ድንቢጥ ፡ ያህላል ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ ቡላል ፡ ያህል ፡ ሆኖ ፡ ያድራል ፡ ባራተኛው ፡ ቀን ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ አድርሶ ፡ ይሄዳል ። አንድም ፡ ሰውነትህን ፡ እንደ ፡ እርኩም ፡ የሚያድሳት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፡ እርኩም ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ከመብል ፡ ተከልክሎ ፡ አፉን ፡ ከደንግያ ፡ ላይ ፡ ያጠራጠሰው ፡ እንደሆነ ፡ እንደ ፡ ዋንጫ ፡ ውልቅ ፡ ብሎ ፡ ይወድቅለታል ፡ ይታደሳል ። አንድም ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ ሰውነትህን ፡ የሚያድሳት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ። (ታሪክ) ፡ እባብ ፡ ብልየት ፡ ያገኘው ፡ እንደ ሆነ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ከምግብ ፡ ተከልክሎ ፡ በሥቁረተ ፡ ዕፅም ፡ በሥቁረተ ፡ ዕብንም ፡ ቢሉ ፡ ሲያልፍ፡ ተገፍፎ፡ይወድቅለታል፡ ይታደሳል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ንስርን፡ እባብ፡ የሚል፡ ንባብ ፡ አልተገኘም ፡ አንድም ፡ ሰውነትህን ፡ በትንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡ የሚያድሳት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው፡ የሚያድሳት ፡ ጌትነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አትርሣ ።

፮ ፣ ገባሬ ፡ ኀይል ፡ እግዚአብሔር ።

ይቅርታን ፡ የሚያደርግ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅርታን ፡ የሚያደርግ ፡ ነው ።

ወይፈትሕ፡ ለኵሉ ፡ ግፉዓን። ኢሳ፡ ፲፩፡፬።

ለተበደሉ ፡ ሁሉ ፡ ይፈርድላቸዋል ፡ አንድም ፡ ለተበደሉ ፡ ለትሩፋን፡ይፈርድላቸዋል፡ ዘፀ ፡ ፳፬፡ ፩፫።

፯ ፣ አርአየ ፡ ፍናዊሁ ፡ ለሙሴ ።

ለሙሴ ፡ ኢታምልክን ፡ ገለጸለት ።

ወለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ሥምረቶ ።

ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ዘጠኙ ን ፡ ሕጋጋት ፡ የገለጸላቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፡ አድሎ ፡ መስጠት ፡ አይ ደለም ፡ ሁሉም ፡ በሁሉ ፡ አሉ ፡ በእግዚእነ ፡ አቡነ እንዳለ ፡

፰ ፡ መሓሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ እግዚአ ብሔር ። ኢዮ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ።

እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ነው ። ይቅር ፡ ባይም ፡ ነው ፡ መዝ ፡ ፻፵፬ ፡ ፰ ርኁቀ ፡ መዓት ፡ ወብዙኃ ፡ ምሕረት ፡ ወጻድቅ ። ዘፀ ፡ ፴፬ ፡ ፮ ፡ ፯ ።

መዓቱ ፡ የራቀ ፡ ቸርነቱ ፡ የቀረበ ፡ ነው ፡ አንድም ፡ መዓቱ ፡ ያነሰ ፡ ቸርነቱ ፡ የበዛ ፡ ነው ፡ (ጻድቅ) ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ኢዮ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ፡ መዝ ፡ ፲፫ ፡ ፳ ፡ ፲፭ ። ያዕ ፡ ፭ ፡ ፲፩ ፡ ፱ ።

፱ ፡ ኢይቀሥፍ ፡ ወትረ ፡ ወኢይትመዓዕ ዘልፈ ።

ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ሰው ፡ በበ ደለው ፡ ቍጥር ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ፈርጄ ፡ ላጥፋ ፡ አይልም ። ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፲፮ ።

፲ ፡ አኮ ፡ በከመ ፡ ኃጢአትነ ፡ ዘገብረ ፡ ለነ

ብነ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ በኃጢአታችን ፡ ልክ ፡ መከራ ፡ ያመጣብነ ፡ አይ ደለም ።

ወኢፈደየነ ፡ በከመ ፡ አበሳነ ።

በታላቁ ፡ ኃጢአታችንም ፡ ልክ ፡ ፍዳ ፡ ያመጣብነ ፡ አይደለም ።

፲፩ ፡ ወበከመ ፡ ልዑል ፡ ሰማይ ፡ እምድር ።

ከምድር ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ሰማይ ፡ ፀንቶ ፡ እንዲኖር ።

አጽንዐ ፡ ምሕረቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕለ እለ ፡ ይፈርህዎ ።

እግዚአብሔር ፡ ለሚፈሩት ፡ ለሚ ያመልኩት ፡ ቸርነቱን ፡ አብዝቶ ፡ አደረገላቸው ። ኢሳ ፡ ፶፭ ፡ ፱ ።

፲፪ ፡ ወበከመ ፡ ይርኅቅ ፡ ሠርቅ ፡ እምዓረብ ።

ከምዕራብ ፡ ምሥራቅ ፡ እንዲርቅ ፡

አርኀቀ ፡ እምኔነ ፡ ኃጢአተነ ።

ኃጢአታችነን ፡ ከኛ ፡ አራቀልን ።

፲፫ ፡ ወበከመ ፡ ይምሕር ፡ አብ ፡ ውሉዶ ።

አባት ፡ ለልጆቹ ፡ እንዲያዝን ፡ እንዲራራ ።

ከማሁ ፡ ይምሕሮሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእለ ፡ ይፈርህዎ ።

እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ለሚፈሩት ፡ ለሚያመል ኩት ፡ ይራራላቸዋል ። ሚል ፡ ፫ ፡ ፲፯። ሉቃ ፡ ፲፭ ፡ ፳ ። ያዕ ፡ ፭ ፡ ፲፩ ።

፲፬ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ የአምር ፡ ፍጥረተነ ።

እሱ ፡ ባሕርያችን ፡ ደካማ ፡ እንደ ሆነ ፡ ያውቃልና ። ተዘከር ፡ ማ ንሻ ፡ አንድም ፡ ባሕርያችን ፡ ደ ካማ ፡ እንደሆነ ፡ ታውቃለህና ፡

ተዘከር ፡ እግዚኦ ፡ ከመ ፡ መሬት ፡ ንሕነ ።

አቤቱ ፡ እኛ ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ እንደሆነ ፡ አስብ ።

፲፭ ፡ ወሰብእሰ ፡ ከመ ፡ ሣዕር ፡ መዋዕሊሁ

መዋዕሊሁ ፡ ለሰብእ ፡ ነው ፤ ሰውስ ፡ ዘመኑ ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ ነው ፤ ያ ፡ ፈጥኖ ፡ ደርቆ ፡ እንዲጠፋ ፡ ፈጥኖ ፡ ይጠፋል ።

ወከመ ፡ ጽጌ ፡ ገዳም ፡ ከማሁ ፡ ይፈሪ ።

ይትነገፍ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እንደ ፡ በረኃ ፡ አበባ ፡ ይረግፋል ፡ ማለት ፡ ያልፋል ፡ ለምልሞ ፡ አብቦ ፡ አፍርቶ ፡ ፈጥኖ ፡ እንዲጠፋ ፡ እንደዚያ ፡ ነው ፡ አንድም ፡ እንደ ፡ ዕፅ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፮ ፡ ፯ ።

፲፮ ፡ እስመ ፡ መንፈስ ፡ ይወፅእ ፡ እምኔሁ ወኢይሄሉ ፡ እንከ ።

ነፍሱ ፡ ከሥጋው፡ ይለያልና ፡ ከቶ የለም ፡ በኋላ ፡ አይመለስምና ።

ወኢየአምር ፡ እንከ ፡ መካኖ ።

ቦታውንም ፡ አያውቀውም ፡ ማለት ፡ ዕትብቱ ፡ የተቆረጠበትን ፡ መካነ ፡ ድማሁን ፡ መካነ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ መካነ ፡ ገሃነምን ፡ አያውቅምና ። ኢዮ ፡ ፲፬ ፡ ፲ ።

፲፯ ፡ ምሕረቱሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምዓለም ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ።

የእግዚአብሔርስ ፡ ይቅርታው ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ ሲደረግ ፡ ይኖራል ።

ዲበ ፡ እለ ፡ ይፈርህዎ ።

ይኸውም ፡ ለማናቸውም ፡ አይደለም ፡ ለሚፈሩት ፡ ለሚያመልኩበት ፡ ነው ።

ወጽድቁኒ ፡ ዲበ ፡ ትውልደ ፡ ትውልድ ።

ቸርነቱም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው ።

ዘፀ ፡ ፴፬ ፡ ፮ - ፯ ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፶ ።

፲፰ ፡ ለእለ ፡ የዓቅቡ ፡ ሕጎ ።

መጽሐፍ ፡ ጭብጡን ፡ አይለቅቅም ፡ ያውም ፡ ሕጉን ፡ ለሚጠብቁ ፡ ነው ።

ወይዜከሩ ፡ ትእዛዞ ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ።

አስቦ ፡ መቅረት ፡ አለና ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ አለ ፡ ይሠሩት ፡ ዘንድ ፡ ሕጉን፡ለሚያስቡ፡ነው። ሲራ ፡ ፲፰ ፡ ፲፩

፲፱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስተዳለወ ፡ መንበሮ ፡ በሰማያት ።

እግዚአብሔር ፡ በሰማይ ፡ ዙፋኑን ፡ አዘጋጀ ፤ በግሥ ፡ ተናገረው ፡ ንጉሥ ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፡ እንዲፈርድ ፡ ይፈርዳል ፡ ሲል ፡ ነው ።

ወኵሉ ፡ ይኴንን ፡ በመንግሥቱ ።

እንደ ፡ ጌትነቱ ፡ ሁሉን ፡ ይገዛል ፡ በሁሉ ፡ ይፈርዳል ።

፳ ፡ ባርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵልክሙ መላእክቲሁ ።

የሰው ፡ አለቆች ፡ መላችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ።

ጽኑዓን ፡ ወኃያላን ፡ እለ ፡ ትገብሩ ፡ ቃሎ

ሕጉን ፡ የምትጠብቁ ፡ ፅኑ ፡ ኃያላ

ንም ፡ የምትሆኑ ፡ ነቢያት ፡ ካህ ናት ፡ አመስግኑት ።

ወእለ ፡ ትሰምዑ ፡ ቃለ ፡ ነገሩ ። ኢሳ ፡ ፷፮ ፡ ፭ ።

ከምስዓል ፡ ከአዕናቍ ፡ የነገሩን ፡ ምሥጢር ፡ የምታውቁ ።

፳፩ ፤ ይባርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵሉ ፡ ኃ ይ ሉ ።

ይኸውም ፡ እላንት ፡ ብቻ ፡ አይ ደላችሁም ፡ ከሀሊነቱን ፡ የሚገ ልጽባቸው ፡ ሠራዊተ ፡ መላእ ክትም ፡ ያመሰግኑታል ።

ላእካኑ ፡ እለ ፡ ይገብሩ ፡ ፈቃዶ ።

ላዕካኒሁ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ሕጉን ፡ አምልኮቱን ፡ የሚጠብቁ ፡ ሊቃነ ፡ መላእክትም ፡ ያመሰግኑታል ።

፳፪ ፤ ይባርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵሉ ፡ ተ ግ ባ ሩ ።

ነጣጣለትና ፡ ፍጥረቶቹ ፡ ሁሉ ፡ እ ግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ።

ውስተ ፡ ኵሉ ፡ በሐውርት ፡ መለኮቱ ።

በሐውርተ ፡ መለኮቱ ፡ ያለ ፡ እንደ ሆነ ፡ ጌትነቱ ፡ መልቶበት ፡ ባለ ፡ ሀገር ፡ ያሉ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፤ በሐ ውርት ፡ መለኮቱ ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ጌትነቱ ፡ ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ ም ሉዕ ፡ ነው ።

ትባርኪ ፡ ነፍስየ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የኔም ፡ ልቡናዬ ፡ እ ግ ዚ አ ብ ሔርን ፡ ታመሰግነዋለች ። ባንዳን ድ ፡ መሥመር ፡ እያገባ ፡ ተናግ ሮት ፡ ነበር ፡ የኋላ ፡ መምህራን ፡ ይበዛል ፡ ይቸካል ፡ ብለው ፡ በመ ጀመሪያና ፡ በመጨረሻ ፡ አድር ገውታል ። ቍ ፡ ፩ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፻፫ ፡ ፩ ፡ ፴፭ ።

መዝሙር ፡ ፻፫ ።

፩ ፤ ትባርኪ ፡ ነፍስየ ፡ ለእግዚአብሔር ። ቍ ፡ ፴፭ ፡ መዝ ፡ ፻፭ ፡ ፩ ፡ ፳-፳፪ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ የሥ ነ ፡ ፍጥረትም ፡ ነገር ፡ አለበት ፤ ሰውነቴ ፡ አንድም ፡ ልቡናዬ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታመሰግነዋለች ።

እግዚእ ፡ አምላኪየ ፡ ጥቀ ፡ ዐበይከ ፡ ፈ ድ ፋ ደ ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ሥራ ፡ ሠርተህ ፡ ፈጽመህ ፡ ከበርህ ።

አሚን ወዕበየ ፡ ስብሐት ፡ ለበስከ ።

ሃይማኖትን ፡ ምግባርን ፡ ወደ ድህ ፡ አንድም ፡ (አሚን) ፡ መታ መንን ፡ (ወዕበየ ፡ ስብሐት) ፡ ዓቢየ ፡ ስብሐት ፡ መባልን ፡ ገን ዘብ ፡ አደረግህ ፤ (ወደድህ) ።

፪ ፤ ወለበስከ ፡ ብርሃነ ፡ ከመ ፡ ልብስ ።

ብርሃንን ፡ እንደ ፡ ሸማ ፡ ተጐናጸ ፍኽ ፡ ማለት ፡ የባሕርይ ፡ ክብ ርን ፡ ገንዘብ ፡ አደረግህ ።

ወረበብኮ ፡ ለሰማይ ፡ ከመ ፡ ሠቅ ። ኤር ፡ ፴ ፡ ፲ ። ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፳ ።

ሰማይን ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ድንኳን ፡ አንድም ፡ እንደ ፡ ገበታ ፡ የዘረጋኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ። ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፩ ። ኤር ፡ ፲ ፡ ፲፪ ። ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፲፪ ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩ ። ፫ ፡ ዘይጠፍር ፡ በማይ ፡ ጽርሖ ።

ዘጠፈረ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ወሀን ፡ አዳራሹን ፡ ያደረገ ፡ አንተ ፡ ነህ ።

ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፯ ፡ ፰ ።

ወረሰየ ፡ ደመና ፡ መከየዶ ።

መመላለሻውን ፡ ደመናን ፡ ያደረገ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ማለት ፡ ምልዓቱን ፡ መናገር ፡ ነው ።

ዘየሐውር ፡ በክንፈ ፡ ነፋስ ።

በነፋስ ፡ ክንፍ ፡ የሚሄድ ፡ አለ ፡ ፍጥነቱን ፡ ሲያይ ። አንድም ፡ የቅጽል ፡ ቅጽል ፡ አድርገህ ፡በነፋስ ፡ ክንፍ ፡ የሚሄድ ፡ ደመናን ፡ መሄጃውን ፡ ያደረገ ፡ ወሀን ፡ አዳራሹን ፡ ያደረገ ፡ አንተ ፡ ነህ ። ፬ ፡ ዘይሬስዮሙ ፡ ለመላእክቲሁ ፡ መንፈሰ ።

መላእክትን፡በርቀት፡ የፈጠራቸው ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወለእለ ፡ ይትለአክዎ ፡ ነደ ፡ እሳት ።

ዘይሬስዮሙ ፡ ለመላእክቲሁ ፡ አለ፡ ይትለአክዎ ፡ መንፈሰ ፡ ወነደ ፡ እሳት ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፤ የሚያገለግሉት ፡ መላእክትን ፡ ከእሳት ፡ ከነፋስ ፡ የፈጠራቸው ፡ እሱ ፡ ነው ። (ሐተታ)፡ የመላእክት ፡ ተፈጥሯቸው ፡ ከእሳት ፡ ከነፋስ ፡ ነውና ፡ ይህስ ፡ አይደለም ፡ ሶበሰ ፡ ተፈጥሩ ፡ እምነፋስ ፡ ወእሳት ፡ እሞቱ ፡ ወእማስኑ ፡ ከማን ፡ ይላል ፡ ብሎ ፡ ተፈጥሯቸው ፡ እምነበ ፡ አልቦ ፡ ነው ፡ ተፈጥሮቶሙሰ ፡ ለመላእክት ፡ እምብርሃን ፡ አምላካዊ ፡ እንዲል ።

ግብራቸውን ፡ ሲያይ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እሳት ፡ ነፋስ ፡ ኃያላን ፡ ረቂቃን ፡ ፈጣኖች ፡ ፈጻምያነ ፡ ፈቃድ ፡ ናቸው ፡ መላእክትም ፡ ኃያላን ፡ ረቂቃን ፡ ናቸውና ፡ ለተልዕኮ ፡ ይፋጠናሉና ፡ የፈጣሪያቸውን ፡ ፈቃድ ፡ ይፈጽማሉና ።

፭ ፡ ሣረራ ፡ ለምድር ፡ ወአጽንዓ ።

ምድርን ፡ አፅንቶ ፡ ፈጠራት ።

ከመ ፡ ኢታንቀልቅል ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለዘላለሙ፡እንዳትናወፅ። ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ።

፮ ፡ ወቀላይኒ ፡ ከመ ፡ ልብስ ፡ አዕፋ ።

ወሀ ፡ እንደ ፡ ሸማ ፡ መጐናጸፍያዋ ፡ ነው ፡ አንድም ፡ ቀላየኒ ፡ ከመ ፡ ልብስ ፡ አዕፀፋ ፡ ይላል ። ወሀን ፡ እንደ ፡ ሸማ ፡ አጐናፀፋት ፡ ወማይ ፡ የዓውዳ ፡ ለምድር ፡ እምኵሉ ፡ ገጸቲሃ ፡ ከመ ፡ ብያዳተ ፡ አንቀቅሆ ፡ የዓውድ ፡ እልመሂሃ ፡ እንዲል ።

ውስተ ፡ አድባር ፡ ይቀውሙ ፡ ማያት ።

ውሆች ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ፀንተው ፡ ይኖራሉ ፡ ማለት ፡ የሥነ ፡ ፍጥረቱን ፡ መናገር ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡ እስከ ፡ ብሩህ ፡ ሰማይ ፡ ድረስ ፡ ወሀ ፡ መልቶ ፡ ነበርና ። ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፱።

፯ ፡ እምተግሣጽከ ፡ ይጎዩ ።

ለይትጋባዕ ፡ ከማለትህ ፡ የተነሣ ፡ ይሸሻሉ ፡ ማለት ፤ ይከፈላሉ ።

ወእምድምፀ ፡ ነጐድጓድከ ፡ ይደነግጹ ። ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፱ ።

እምተግሣፅከ ፡ ወእምድምፀ ፡ ነጐድጓድከ ፡ ይጎዩ ፡ ወይደነግጹ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ ከቃልህ ፡ መሰማት ፡ የተነሣ ፡ ይደነግጻሉ ።

፰ ፡ የዐርጉ ፡ አድባረ ፡ ይወርዱ ፡ ገዳመ ።

ወደ ፡ ተራራ ፡ ይወጣሉ ፡ ወደ ፡ በረኃ ፡ ይወርዳሉ ፡ ይጎዩ ፡ ወይደነግጹ ፡ ያለውን ፡ ደገመው ፤ ውስተ ፡ ብሔር ፡ ኀበ ፡ ሣረርኮሙ ፡ ወሠራዕኮሙ ፡ ወደ ፡ ሠራህላቸው ፡ ወደ ፡ ወሰንህላቸው ፡ ቦታ ። ኢሳ ፡ ፴፱ ፡ ፲፰ ።

፱ ፡ ወሰኖሙኒ ፡ እምኀበ ፡ ኢየኃልፉ ።

ወሰናቸውም ፡ ከማይተላለፉበት ፡ ነው ፤ አንድም ፡ (አጥብቀህ ፡ አንቀጽ ፡ አድርገህ) ፡ ከማይተላለፍበት ፡ ወሰናቸው ፡ ብለህ ፡ ዕሠር ። ኢዮ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።

ከመ ፡ ኢይትመየጡ ፡ ወኢይክድንዋ ፡ ለምድር ።

ተመልሰው ፡ ይህቺን ፡ ዓለም ፡ እንዳያለብሷት ፡ አንድም ፡ ውስተ ፡ (አድባር ፡ ይቀውሙ ፡ ማያት) ፡ አንቅዕት ፡ በደጋ ፡ ይጀምራሉ ። (እምተግሣፅከ ፡ ወእምድምፀ ፡ ነጐድጓድከ ፡ ይጎዩ ፡ ወይደነግፁ ፡ የዐርጉ ፡ አድባረ ፡ ወይወርዱ ፡ ገዳመ) ፡ ከመፍረድህ ፡ የተነሣ ፡ ከደጋ ፡ ወደ ፡ ቈላ ፡ ይወርዳሉ ፡ (ውስተ ፡ ብሔር ፡ ኀበ ፡ ሣረርኮሙ ፡ ወሠራዕኮሙ) ፡ ወደ ፡ ሠራህላቸው ፡ ወደ ፡ ወሰንህላቸው ፡ ወደ ፡ ቈላ ፡ (ወሰኖሙኒ ፡ ከመ ፡ ኢይትመየጡ) ፡ እንዳለፈው ። አንድም ፡ (ውስተ ፡ አድባር) ፡ ዝናማት ፡ መዝነም ፡ ከደጋ ፡ ይጀምራሉ ፡ (እምተግሣፅከ) ፡ ከመፍረድህ ፡ የተነሣ ፡ እየዘነሙ ፡ ከደጋ ፡ ወደ ፡ ቈላ ፡ ይወርዳሉ ፡ (ውስተ ፡ ብሔር) ፡ ወደ ፡ ሠራህላቸው ፡ ወደ ፡ ወሰንህላቸው ፡ ወደ ፡ ቈላ ፡ ይወርዳሉ ፤ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ወሀ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ይወርዳል ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አይወጣምና ፡ (ወሰኖሙኒ ፡ ከመ ፡ ኢይትመየጡ ፡ እንዳለፈው ።

አንድም ፡ (ውስተ ፡ አድባር) ፡ በሐምሌ ፡ በነሐሴ ፡ ተራራ ፡ ተራራ ፡ ያህል ፡ እየሆነ ፡ ማዕበል ፡ ሞገዱ ፡ ይነሣል ። እምተግሣፅከ) ፡ ከመፍረድህ ፡ የተነሣ ፡ ይሸሻሉ ፡ ወደ ፡ ቈላ ፡ ይወርዳሉ ፡ ማለት ፤ በኅዳር ፡ በታኅሣሥ ፡ ይጎ

ድላሉ ፡ (ውስተ ፡ ብሔር) ፡ ወሰና
ሙኒ ፡ እንዳለፈው ። (ከመ ፡ ኢይ
ትመየጡ) ፡ ተመልሰው ፡ ይህችን ፡
ዓለም ፡ እንዳያለብሷት ፡ ማለት ፤
ምንም ፡ ቢሆን ፡ ወሀ ፡ ከቂሊሙ ፡
አያልፍምና ።

አንድም ፡ (ውስተ ፡ አድባር) ፡
ትሩፋን ፡ በባቢሎናውያን ፡ እጅ ፡
ተማርከው ፡ ባቢሎን ፡ ወርደው ፡
ሰባ ፡ ዘመን ፡ ይኖራሉ ፡ (እምተ
ተግሣፅከ) ፡ ወእምድምፀ ፡ ነጐ
ድጓድከ) ፡ አንተ ፡ ከመፍረድህ ፡
የተነሣ ፡ ተማርከው ፡ ባቢሎን ፡
ይወርዳሉ ፡ (የዓርጉ) ፡ ንጉሠ ፡ ነገ
ሥት ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ይሆናሉ ።
(ወይወርዱ) ፡ ቋሚ ፡ ለጓሚ ፡
ይሆናሉ ፡ (ውስተ ፡ ብሔር) ፡
ሰባ ፡ ዘመን ፡ ይኖሩባት ፡ ዘንድ ፡
በወሰንህላቸው ፡ በባቢሎን ፡ (ወሰ
ኖሙኒ) ፡ ከማይተላለፉበት ፡ ከባ
ቢሎን ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ወሰናቸው ።
(ከመ ፡ ኢይትመየጡ) ፡ ሰብዓ ፡
ዘመን ፡ ሳይፈጸም ፡ ተመልሰው ፡
ኢየሩሳሌምን ፡ እንዳይወርሷት ።

፲ ፡ ዘይፌኑ ፡ አንቅዕተ ፡ ውስተ ፡ ቈላት ።

አንዱን ፡ ይዞ ፡ ይሄዳል ፡ ምንጬ
ን ፡ ከደጋ ፡ ወደ ፡ ቈላ ፡ እንዲሄድ ፡
የሚያደርገው ፡ እሱ ፡ ነው ፤ አን
ድም ፡ ትሩፋንን ፡ ተማርከው ፡ ከኢ
የሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ እንዲ
ወርዱ ፡ የሚያደርግ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ማዕከለ ፡ አድባር ፡ የኀልፉ ፡ ማያት ።

ውሆች ፡ በወሀና ፡ በወሀ ፡ መካከ
ል ፡ አንድም ፡ በተራራና ፡ በተራ
ራ ፡ መካከል ፡ ይሄዳሉ ፡ ምንም፡
ቢሆን ፡ ወሀ ፡ ዙሮ ፡ ይሄዳል ፡
እንጂ ፡ ተራራውን ፡ ሠንጥቄ ፡
ልሂድ ፡ አይልምና ። አንድም ፡ ት
ሩፋን፡ በኃያላኑ ፡ እጅ ፡ ተይዘው ፡
ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ይወርዳሉ ።

፲፩ ፡ ወያሰትዩ ፡ ለኵሉ ፡ አርዌ ፡ ገዳም ።

ውሀነታቸውን ፡ በበረሀ ፡ ላሉ ፡
አራዊት ፡ ሁሉ ፡ ያጠጣሉ ። አን
ድም ፡ ትሩፋን ፡ ገንዘባቸውን ፡
ለአሕዛብ ፡ ይሰጣሉ ።

ወይትዌከፉ ፡ ሐል (ለ) ስትዮታት ፡
ለጽምዖሙ ።

ሐለስትዮ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
የበዳ ፡ አህያ ፡ ሐልስትዮ ፡ ያለ ፡
እንደሆነ ፡ ጠጣ ፡ ነው ፡ ጥማቸ
ውን ፡ ለማራቅ ፡ ወሀውን ፡ ይጠ
ጣሉ ፤ በሐለስትዮታት ፡ ሁሉን ፡
መናገር ፡ ነው ። አንድም ፡ በል
ተው ፡ ጠጥተው ፡ ንዴታቸውን ፡
ለማራቅ ፡ አሕዛብ ፡ የትሩፋንን ፡
ገንዘብ ፡ ይቀበላሉ ።

፲፪ ፡ ወያጽሉ ፡ ህየ ፤ አዕዋፈ ፡ ሰማይ ።

የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ከወሀው ፡ ዳር ፡
ያርፋሉ ፡ አንድም ፡ ትሩፋን ፡ ሰባ ፡
ዘመን ፡ ይኖራሉ ።

ወይነቅዉ ፡ በማዕከለ ፡ ያላዕት ።

በዋሻው ፡ መካከል ፡ ተቀምጠው፡

ይጮኻሉ ፤ ከወሀ ፡ ዳር ፡ ዛፍ ፡ ገደል ፡ አይታጣምና ፡ ከዚያ ፡ ተቀም ጠው ፡ ጭው ፡ ጭው ፡ ይላሉ ። አንድም ፡ ትሩፋን ፡ በባቢሎን ፡ መከራ ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ሲያለቅ ሱ ፡ ይኖራሉ ። ዘፍ ፤ ፩ ፡ ፳፱ - ፴፩ ። ኢሳ ፲፫ ፡ ፳፩ - ፳፪ ።

፲፫ ፤ ዘይሠቅዮሙ ፡ ለአድባር ፡ እም ው ማጥያቲሆሙ ።

ተራሮችን ፡ ውስጥ ፡ ውስጣቸውን ፡ የሚያጠጣቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ባያ ጠጣቸው ፡ እንደ ፡ ጐተራ ፡ በፈረ ሱ ፡ ነበርና ፡ ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ድርቅ ፡ በሆነ ፡ ዘመን ፡ ተራራው ፡ ሲናድ ፡ ይታያል ፤ አንድም ፡ ነገ ሥታቱን ፡ በነቢያት ፡ በካህናት ፡ አድሮ ፡ የሚያስተምራቸው ፡ እሱ ፡ ነው ።

እምፍሬ ፡ ተግባርከ ፡ ትጸግብ ፡ ምድር ። ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፳፩ ።

ተግባር ፡ ደመና ፡ ፍሬ ፡ ዝናም ፡ ነው ፤ ትፀግብ ፡ ምድር ፡ ፍሬ ፡ እምተግባ ርከ ፡ ይላል ፤ ምድር ፡ ከደመና ፡ የተገኘውን ፡ ዝናም ፡ ትረካለች ።

፲፬ ፤ ዘያበቊል ፡ ሣዕረ ፡ ለእንስሳ ።

ለእንስሳ ፡ ምግብ ፡ ሊሆን ፡ ሣርን ፡ የሚያበቅል ፡ ዝናም ፡ ነው ፤ አን ድም ፡ ጌታ ፡ ነው ።

ወሐመልማለ ፡ ለቅኔ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው

ለሰው ፡ ለሚገዛ ፡ ለእንስሳ ፡ ልም ላሜ ፡ ያለውን ፡ የሚያበቅል ፡ ዝናም ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ጌታ ፡ ነው ። አንድም ለእግዚአብሔር ፡ ለሚገዛ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ እህሉን ፡ ተክሉን ፡ የሚያበቅል ፡ ዝናም ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ጌታ ፡ ነው ። አን ድም ፡ እህልን ፡ ተክልን ፡ የሚ ያበቅል ፡ ጌታ ፡ ነው ፤ (ለቅኔ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው) ፡ ሰው ፡ ያን ፡ እየበላ ፡ ለመግዛት ።

ከመ ፡ ያውፅእ ፡ እክለ ፡ እምድር ።

እምፍሬ ፡ ተግባርከ ፡ ትፀግብ ፡ ምድር ፡ ብሎ ፡ ነበርና ። ቍ ፡ ፲፫ ።

ከምድር ፡ ሁሉን ፡ ያበቅል ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ፡ ፴ ፡ ፱ ፡ ፫ ። ኢዮ ፡ ፴፰ ፡ ፳፯ ፡ ፳፯ ። ኢሳ ፡ ፴ ፡ ፳፫ ፡ ፵፱ ፡ ፳ ።

፲፭ ፤ ወይን ፡ ያስተፌሥሕ ፡ ልበ ፡ ሰብእ ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፳ ፡ ፳፫ ።

ወይን ፡ የሰውን ፡ ልቡና ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ፤ አንድም ፡ ወይን ፡ መፈ ጠሩ ፡ ለከንቱ ፡ አይደለም ፡ የሰ ውን ፡ ልቡና ፡ ደስ ፡ ሊያሰኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ወቅብዕ ፡ ለአብርሆ ፡ ገጽ ።

ዘይትም ፡ የሰውን ፡ መልክ ፡ ብ ሩህ ፡ መልአክ ፡ ያስመስላል ፡ አንድም ፡ ዘይት ፡ መፈጠሩ ፡ ለከ ንቱ ፡ አይደለም ፡ የሰውን ፡ መል ክ ፡ ብሩህ ፡ መልአክ ፡ ሊያስመ ስል ፡ ነው ፡ እንጂ ።

እክል ፡ ያጸንዕ ፡ ኃይለ ፡ ሰብእ ።

እህል ፡ የሰውን ፡ ኃይል ፡ ያፀናል ።

አንድም ፡ እህል ፡ መፈጠሩ ፡ ለከ
ንቱ ፡ አይደለም ፡ የሰውን ፡ ኃይ
ል ፡ ለማፅናት ፡ ነው ፡ እንጂ ።
አንድም ፡ (ወይን ፡ ያስተፌሥሕ ፡
ልበ ፡ ሰብእ) ፡ ደሙ ፡ ልበ ፡ ነፍ
ስን ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ። አንድም ፡
ደሙ ፡ መሰጠቱ ፡ ለከንቱ ፡ አይ
ደለም ፡ ልበ ፡ ነፍስን ፡ ደስ ፡ ሊያ
ሰኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ። (ወቅብዕ ፡
ለእብርሆ ፡ ገጽ)፡ መንፈስ ፡ ቅዱ
ስ ፡ ሰውን ፡ ብሩህ ፡ መልአክ ፡ ያ
ስመስላል ። አንድም ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ መሰጠቱ ፡ ለከንቱ ፡ አይ
ደለም ፤ ብሩህ ፡ መአልክ ፡ ሊያስ
መስል ፡ ነው ፡ እንጂ ። (ዕክል ፡
ያፀንዕ ፡ ኃይለ ፡ ሰብእ) ፡ ሥጋው ፡
ኃይለ ፡ ነፍስን ፡ ያፀናል ፡ አን
ድም ፡ ሥጋው ፡ መሰጠቱ ፡ ለከ
ንቱ ፡ አይደለም ፡ ኃይለ ፡ ነፍ
ስን ፡ ሊያፀና ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፲፮ ፤ ወይጸግቡ ፡ ኵሉ ፡ ዕፀወ ፡ ገዳም ።

በበረኃ ፡ የሚኖሩ ፡ ዕፀዋት ፡ ሁሉ ፡
ዝናሙን ፡ ልምላሜውን ፡ ይረካ
ሉ ፡ አንድም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እህሉን ፡
ተክሉን ፡ በልተው ፡ ደስ ፡ ይላ
ቸዋል ። አንድም ፡ ምዕመናን ፡
ሁሉ ፡ ልጅነትን ፡ አግኝተው ፡
ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ተቀብለው ፡
ደስ ፡ ይላቸዋል ።

አርዘ ፡ ሊባኖስ ፡ ዘተከልከ ።

የደጋውን ፡ ዛፍ ፡ የፈጠርህ ፡
አንተ ፡ ነህ ። አንድም ፡ የደጋ
ውን ፡ ዛፍ ፡ የፈጠርህ ፡ ለከንቱ ፡
አይደለም ፡ የአዕዋፍ ፡ ማደሪያ ፡
ሊሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ። አንድም ፡
አብርሃምን ፡ የፈጠርኸ ፡ አንተ ፡
ነህ ፤ አብርሃምን ፡ የፈጠርኸ ፡
ለከንቱ ፡ አይደለም ፡ የሁሉ ፡
አባት ፡ ሊሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፲፯ ፤ ወበህየ ፡ ይትዋለዱ ፡ አዕዋፍ ።

በዛፉ ፡ ላይ ፡ አዕዋፍ ፡ ይራባሉ ፡
አንድም ፡ ከአብርሃም ፡ እስራኤ
ልም ፡ አሕዛብም ፡ ይወለዳሉ ።

ወይትጋወርን ፡ ቤተ ፡ ሄሮድያኖስ ።

የሄሮድያኖስ ፡ ወገን ፡ ይጎራበታቸ
ዋል ፡ ማለት ፤ ይህ ፡ ሰንሁት ፡ የሚ
ባል ፡ ዘንዶ ፡ ነው ፡ ዘቦ ፡ ክን
ፍ ፡ ይለዋል ፡ አይመጥቅለትም ፡
እንጂ ፡ ከዛፍ ፡ ስር ፡ ሁኖ ፡ እ
ንቍላላቸውን ፡ ያበላሽባቸዋል ፡
ይሠብርባቸዋል ። አንድም ፡ ናቡ
ከደነፆር ፡ ይጎራበታቸዋል ፡ ማለ
ት ፤ ይማርካቸዋል ።

፲፰ ፡ አድባር ፡ ነዋኃት ፡ ለኃየላት ።

ረጃጅሙን ፡ ተራራ ፡ መፍጠሩ ፡
የዋልያ ፡ ማደሪያ ፡ ሊሆን ፡ ነው ።
አንድም ፡ አብርሃምን ፡ መፍጠ
ሩ ፡ ያሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡ እስ
ራኤል ፡ አባት ፡ ሊሆን ፡ ነው ።
አንድም ፡ ለከንቱ ፡ አይደለም ፤
ያሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡ እስራ

ኤል ፡ አባት ፡ ሊሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡

ወያላስት ፡ ምጕያዮን ፡ ለግሔ ። ኢዮ ፡ ፴፯ ፡ ፰ ።

ዋሻው ፡ መፈጠሩ ፡ ለግሔያት ፡ (ለአሽኮኮዎች) ፡ መኖሪያ ፡ መሸሻ ፡ ሊሆን ፡ ነው ። አንድም ፡ ለከንቱ ፡ አይደለም ፡ ለግሔያት ፡ መኖሪያ ፡ መሸሻ ፡ ሊሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፲፱ ፤ ወገበርከ ፡ ወርኀ ፡ በዕድሜሁ ።

ጨረቃን ፡ በምልዓት ፡ ፈጠርህ ።

ፀሐይኒ ፡ አእመረ ፡ ምዕራቢሁ ።

ፀሐይም ፡ መግቢያውን ፡ ዐወቀ ። በምዕራብ ፡ ተፈጥሯልና ፡ አንድም ፡ በምሥራቅ ፡ ስድስት ፡ በምዕራብ ፡ ስድስት ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ መሳክው ፡ አሉት ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የኔ ፡ ገንዘብ ፡ ከሆነ ፡ ብሎ ፡ ያለ ፡ ጊዜው ፡ ልሒድበት ፡ አይልምና ፤ አንድም ፡ ደክሞ ፡ ከመንገድ ፡ ልደር ፡ አይልምና ።

፳ ፤ ታመጽእ ፡ ጽልመተ ፡ ወይከውን ፡ ሌሊተ ።

ጭለማን ፡ ታመጣለህ ፤ ሌሊት ፡ ይሆናል ። አንድም ፡ ዔዋዌን ፡ ታገዛለህ ፡ ይደረጋል ።

ወይወጽኡ ፡ ቦቱ ፡ ኵሉ ፡ አርዌ ፡ ገዳም ።

በበረሃ ፡ የሚኖሩ ፡ አራዊት ፡ ሁሉ ፡ ይሠማራሉ ።

፳፩ ፤ ዕጕለ ፡ አናብስት ፡ ይጥሕሩ ፡ ወይመሥጡ ።

ያንበሳ ፡ ገላግልት ፡ እየሩኹ ፡ ምግባቸውን ፡ ይነጥቃሉ ። አንድም ፡ አሕዛብ ፡ እየፎከሩ ፡ ይማርካሉ ።

ወይስእሉ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲሳዮሙ ።

ምግባቸውንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይለምናሉ ፡ ማለት ፤ እንዲያሻቸው ፡ አውቆ ፡ መስጠቱን ፡ መናገር ፡ ነው ። አንድም ፡ እሱ ፡ ባወቀ ፡ ይለምኑታልና ። አንድም ፡ አሕዛብ፡ይለምኑታል፡ይሰጣቸዋል ።

፳፪ ፤ ወእምከመ ፡ ሠረቀ ፡ ፀሐይ ፡ የአትዉ ።

ፀሐይ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ አራዊት ፡ ወደ ፡ በዓታቸው ፡ ይገባሉ ። አንድም ፡ ሚጠት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ አሕዛብ ፡ ይጠፋሉ ።

ወይውዕሉ ፡ ውስተ ፡ ግበቢሆሙ ።

በየፍርኳታቸው ፡ በየዋሻቸው ፡ ገብተው ፡ ይውላሉ ፤ እንዘ ፡ ይቈርሩ ፡ ይላል ፡ ኢዮብ ፡ ሲፈሩ ፡ ሲንቀጠቀጡ ፡ ይውላሉ ። አንድም ፡ አሕዛብ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ይወርዳሉ ።

፳፫ ፤ ወይወፅእ ፡ ሰብእ ፡ ውስተ ፡ ተግባሩ ።

ፀሐይ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ይሠማራል ።

ይወፅእ ፡ ወይትቀነይ ፡ እስከ ፡ ይመሲ ።

ሰው ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ይሠማራል ፡ (ይወፅእ) ፡ እስኪመሽ ፡ ሲሠራ ፡ ይውላል ።

፳፬ ፡ ጥቀ ፡ ዐቢይ ፡ ግብርከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ ሥራህ ፡ እጅግ ፡ ድንቅ ፡ ነው ። መዝ ፡ ፻፳ ፡ ፭ ። ሲራ ፡ ፲፯ ፡ ፴ ።

ወኵሎ ፡ በጥበብ ፡ ገበርከ ።

ሰውን ፡ በመዓልት ፡ እንጂ ፡ በሌሊት ፡ እንዳይሠማራ ፡ አራዊትን ፡ በሌሊት ፡ እንጂ ፡ በመዓልት ፡ እንዳ ይሠማሩ ፡ ወሰንህ ፤ አንድም ፡ የወሰንህ ፡ አንተ ፡ ነህ ። ከሰው ፡ በቀር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ያፈረሰ ፡ የለም ፡ ሁሉም ፡ እሱ ፡ በወሰናቸው ፡ ይኖራሉ ፤ ሰው ፡ ግን ፡ ጨለማ ፡ ለብሶ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ ይሄዳልና ። አንድም ፡ ሰውን ፡ አቅንቶ ፡ መፍጠሩ ፡ ትንሣኤ ፡ አላችሁ ፡ አራዊትን ፡ አስጎንብሶ ፡ መፍጠሩ ፡ ትንሣኤ ፡ የላችሁም ፡ ሲል ፡ ነውና ።

መልአ ፡ ምድረ ፡ ዘፈጠርከ ።

የፈጠርኸው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ምድርን ፡ መላ ፡ ምልዓ ፡ ምድር ፡ ሆነ ። ኢሳ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱ - ፳፱ ።

፳፭ ፡ ዛቲ ፡ ባሕር ፡ ዐባይ ፡ ወረኃብ ።

ይህቺ ፡ ባሕር ፡ ውቅያኖስ ፡ የወርድ ፡ የቁመት ፡ ሰፊ ፡ ናት ።

ህየ ፡ ዘይትሐወስ ፡ ዘአልቦ ፡ ኍልቈ

በውቅያኖስ ፡ ያለ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ሥፍር ፡ ቍጥር ፡ የለውም ።

እንስሳ ፡ ዐበይት ፡ ምስለ ፡ ደቃቅ ።

ታላላቁ ፡ ከታናናሹ ፡ ጋራ ፡ ማለት ፡ ዓሣ ፡ ዓንበሪ ፡ አዞ ፡ ጉማሬ ፡ ሁሉ ።

፳፮ ፡ ህየ ፡ የሐውራ ፡ አሕማር ።

በባሕር ፡ ላይ ፡ መርከቦች ፡ ይሄዳሉ ። ወፈቀዳ ፡ ይሠጠማ ፡ አሕማር ፡ እንዲል ።

ከይሲ ፡ ዘፈጠርከ ፡ ይሣለቅ ፡ ላዕሌሆሙ ።

የፈጠርኸው ፡ ዘንዶ ፡ በሳቸው ፡ ይዘብትባቸዋል ። ሰፌዶ ፡ የሚባል ፡ መልኩ ፡ ባሕር ፡ የሚመስል ፡ ዘንዶ ፡ አለ ፡ ነጋድያን ፡ በመርከብ ፡ ተጭነው ፡ ሲሄዱ ፡ ማዕበሉን ፡ መስሎ ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ መጥቶ ፡ መርከባቸውን ፡ ይበሳዋል ፡ ይሰጥማሉ ፤ ከዚያ ፡ ሆኖ ፡ ይመገባቸዋልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። አንድም ፡ (ዛቲ ፡ ባሕር) ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የቁመት ፡ የወርድ ፡ ሰፊ ፡ ናት ። (ህየ ፡ ዘይትሐወስ) ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡ እስራኤል ፡ ሥፍር ፡ ቍጥር ፡ የላቸውም ፡ (እንስሳ) ፡ ታላላቁ ፡ ከታናናሹ ፡ ጋራ ፡ የዕድሜ ፡ የማዕርግ ፡ ነው ፡ (ህየ ፡ የሐውራ) ፡ አሕዛብ ፡ ይዘምቱበታል ። አሌሎን ፡ ለአሕማር ፡ እለ ፡

ቦን ፡ ክንፍ ፡ እንዲል ፡ ሊሳ ፡ (ከይሲ፡ ዘፈጠርከ) ፡ ናቡከደነፆር ፡ ይማርካቸዋል ።

እንድም ፡ (ዛቲ ፡ ባሕር) ፡ ይህቺ ፡ ዓለም ፡ የቁመት ፡ የወርድ ፡ ሰፊ ፡ ናት ፡ (ህየ ፡ ዘይትሐወስ) ፡ በዚች ፡ ዓለም ፡ የሚኖር ፡ ፍጥረት ፡ ሥፍር ፡ ቍጥር ፡ የለውም ፤ (እንስሳ) ፡ ታላላቁ ፡ ከታናናሹ ፡ ጋራ ፡ (ህየ) ፡ ነቢያት ፡ ይመግቧቸዋል ። (ከይሲ) ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የፈጠርኸው ፡ ዲያብሎስ ፡ እቈራኛቸዋለሁ ፡ ይላል ።

እንድም ፡ (ዛቲ ፡ ባሕር) ፡ ጥምቀት ፡ ሰፊ ፡ ናት ፡ ማለት ፡ ጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ መድረሷን ፡ መናገር ፡ ነው ። (ህየ) ፡ በጥምቀት ፡ ያመኑ ፡ ምዕመናን ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። (እንስሳ)፡ ታላላቁ፡ ከታናናሹ፡ ጋራ፡ የዕድሜ ፡ የማዕርግ ፡ ትንሹም ፡ ትልቁም ፡ ያርባ ፡ የሰማንያ ፡ ቀን ፡ ያርባ ፡ የሰማንያ ፡ ዘመን ፡ ይጠመቃልና ። (ህየ) ፡ ሐዋርያት ፡ ይመግቧታል ፡ (ከይሲ) ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዲያብሎስ ፡ እቈራኛቸዋለሁ ፡ ይላል ፤ አይሆንለትም ፡ እንጂ ፡ ኢሳ ፡ ፳፯ ፡ ፩ ።

፳፯ ፡ ወኵሎሙ ፡ ይሴፎ ፡ በኀቤከ ።

ሰው ፡ ሁሉ ፡ አንተን ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋል ።

ተሀበሙ ፡ ሲሳዮሙ ፡ በጊዜሁ ።

ምግባቸውን ፡ በየጊዜው ፡ ትሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ማለት ፤ በዘር ፡ ጊዜ ፡ ዘሩን ፡ በመከር ፡ ጊዜ ፡ መከሩን ።

፳፰ ፡ ወእምከመ ፡ ወሀብኮሙ ፡ ያስተጋብኡ ።

ከሰጠኻቸውም ፡ በኋላ ፡ በሬቅ ፡ በጎታ ፡ በጎተራ ፡ ይሰበስባሉ ፡ አንድም ፡ ለሰው ፡ አይሰጡም ፡ ጭብጥ ፡ አድርገው ፡ ይይዛሉ ።

ወፈቲሐከ ፡ እዴከ ፡ ታጸግብ ፡ ለኵሉ ፡ እምሕረትከ ።

አንተ ፡ ግን ፡ እጅ ፡ ሰፊ ፡ ነህና ፡ እጅህን ፡ ዘርግተህ ፡ ከቸርነትህ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ምግባቸውን ፡ ሰጥተህ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ታሰኛለህ ፡ መዝ ፡ ፻፵፬ ፡ ፲፭ ። ማቴ ፡ ፮ ፡ ፳፰ ። ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፮ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፯ ።

፳፱ ፡ እመሰ ፡ ሜጥከ ፡ ገጸከ ፡ ይደነግፁ ።

ለጊዜው ፡ ገጸ ፡ መዓትህን ፡ ብትመልሰው ፡ ግን ፡ በመከራው ፡ በረኃቡ ፡ ይደነግጣሉ ።

ትወጽእ ፡ መንፈሶሙ ፡ ወይገብኡ ።

ነፍሳቸው ፡ ከሥጋቸው ፡ በረኃቡ ፡ እለየዋለሁ ፡ ትላለች ፤ (ወየሐልቁ) ፡ አለቅን ፡ አለቅን ፡ ይላሉ ።

ወይገብኡ ፡ ውስተ ፡ መሬቶሙ ።

ኢዮ ፡ ፲፬ ፡ ፲፬ ፡ ፳ ።

ወደ ፡ መሬታቸው ፡ (መሬትነታቸው) ፡ ይመለሳሉ ። ሲራ ፡ ፲፯ ፡ ፩

፴ ፤ ትፌኑ ፡ መንፈስከ ፡ ወይትፈጠሩ ።

ኋላ ፡ ግን ፡ ዝናም ፡ የቋጠረ ፡ ደመናን ፡ የያዘ ፡ ነፋስን ፡ ታመጣለህ ፡ በዝናም ፡ የበቀለውን ፡ እህሉን ፡ ተክሉን ፡ በልተው ፡ ይታደሳሉ ።

ወትሔድስ ፡ ገጻ ፡ ለምድር ።

ምድርን ፡ በልምላሜ ፡ ታድሳታለህ ፤ ለሰስ ፡ ያለ ፡ ዝናም ፡ የወረደ ፡ እንደሆነ ፡ ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፏ ፡ ብላ ፡ ትበቅላለችና ። አንድም ፡ ትሩፋን ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በሚጠት ፡ ደስ ፡ ታሰኛታለህ ።

አንድም ፡ (ታወፅእ ፡ መንፈሶሙ) ፡ ነፍሳቸውን ፡ ከሥጋቸው ፡ በሞት ፡ ትለያታለህ ። (የሐልቁ) ፡ ይፈጸማሉ ። (ወይገብኡ) ፡ ወደ ፡ መሬትነታቸው ፡ ይመለሳሉ ። መሬት ፡ አንተ ፡ ወትገብዕ ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡ እንዲል ፡ (ትፌኑ) ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ታሳድርባቸዋለህ ፡ ታድሰው ፡ ይነሣሉ ። (ወትሔድስ) ፡ ምዕመንን ፡ በትንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡ ታድሳታለህ ።

፴፩ ፤ ለይኩን ፡ ስብሐቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለዓለም ።

የእግዚአብሔር ፡ ጌትነቱ ፡ ለዘላለሙ ፡ ሲመሰገን ፡ ይኑር ፡ (ይኖራል) ።

ይትፌሣሕ ፡ እግዚአብሔር ፡ በተግባሩ ፡

እግዚአብሔር ፡ በፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ ደስ ፡ የማያሰኝ ፡ ፍጥረት ፡ አልፈጠረምና ፡ በእንቢተኛነቱ ፡ ይቀርበታል ፡ እንጂ ።

፴፪ ፤ ዘይኔጽራ ፡ ለምድር ፡ ወይሬስያ ፡ ከመ ፡ ትርዓድ ።

በዌዋዌ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ በሚጠት ፡ ጊዜ ፡ ባቢሎንን ፡ ትፈታ ፡ ዘንድ ፡ በዓይነ ፡ መዓት ፡ የሚያያት ፡ እሱ ፡ ነው ። አንድም ፡ ታልፍ ፡ ዘንድ ፡ ይህቺን ፡ ዓለም ፡ በዓይነ ፡ መዓት ፡ የሚያያት ፡ እሱ ፡ ነው ።

ዘይገሥሦሙ ፡ ለአድባር ፡ ወይጠይሱ ።

ነገሥታቱን ፡ በኵርናዓ ፡ መዓቱ ፡ የሚዳስሳቸው ፡ እሱ ፡ ነው ። (ይጠይሱ) ፡ ይጠፋሉ ፤ ይጢሱ ፡ ይጠፉ ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ ተራሮችን ፡ በእደ ፡ ኀልፈት ፡ የሚዳስሳቸው ፡ እሱ ፡ ነው ። ያልፋሉ ፤ ያልፉ ፡ ዘንድ ።

፴፫ ፤ እሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሕይወትየ ።

እግዚአብሔርን ፡ ባለ ፡ ዘመኔ ፡ ሁሉ ፡ አመሰግነዋለሁ ፡ መዝ፡ ፻፵፭፡፪

ወእዜምር ፡ ለአምላኪየ ፡ በአምጣነ ፡ ሀሎኩ ።

ለፈጣሪዬ ፡ በዕድሜዬ ፡ ልክ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

፴፬ ፤ ወእሠምር ፡ በቃልየ ።

ቃልየም ፡ ቢል ፡ በ ፡ ብለህ ፡ ተር

ጉም ፤ በቃሌም ፡ ደስ ፡ አሰኘዋለሁ ።

ወአንሰ ፡ እትፌሣሕ ፡ በእግዚአብሔር ዕን ፡ ፫ ፡ ፲፰ ።

እኔ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እምኜ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

፴፭ ፤ ወየኀልቁ ፡ ኃጥኣን ፡ እምድር ።

ኃጥአን ፡ ግን ፡ አንድም ፡ ባቢሎናውያን ፡ ግን ፡ ከሰው ፡ ተለይቶው ፡ አንድም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ይጠፋሉ ፡ ይጥፉ ።

ወዐማፅያንሂ ፡ ኢይሄልዉ ፡ እንከ ።

ዐመፀኞችም ፡ በ.ኖሩ ፡ በ.ኖሩ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ የኖሩትን ፡ ያህል ፡ አይኖሩም ።

ትባርኮ ፡ ነፍስየ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቀ ፡ ፩ ።

ሰውነቴ ፡ አንድም ፡ ልቡናዬ ፡ እግዚአብሔርን ታመሰግነዋለች ።

መዝሙር ፡ ፻፬ ።

ሃሌ ፡ ሉያ ።

ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበረ ፡ ዓለምን ፡ አሳልፎ ፡ የሚኖር ፤ አንድም ፡ ያህ ፡ ይላል ፡ በዓረብ ፡ ስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፩ ፤ ግነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወጸውዑ ፡ ስሞ

ስሙን ፡ እየጠራችሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምስጋና ፡ የሃይማኖት ፡ አገዛዝ ፡ ተገዙ ።

ወንግርዎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ምግባሮ ።

ከሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ጀምሮ ፡ ያደረገውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራውን ፡ ለአሕዛብ ፡ ንገሯቸው ፤ አስተምሯቸው ።

፪ ፤ ሰብሕዎ ፡ ወዘምሩ ፡ ሎቱ ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ እሱን ፡ አመስግኑት ፡ ለስሙም ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ።

ወንግሩ ፡ ኵሎ ፡ መንክሮ ። ኢሳ ፡ ፲፪ ፡ ፬ ። ፳፯ ፡ ፲፫ ።

ድንቅ ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ ንገሩ ፤ አስተምሩ ።

፫ ፤ ወትከብሩ ፡ በስሙ ፡ ቅዱስ ።

እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ የሚሆን ፡ ስሙን ፡ በማመስገን ፡ (ለስሙ) ፡ ለማመስገን ፡ ትከበራላችሁ ።

ለይትፌሣሕ ፡ ልብ ፡ ዘየኀሥሥ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የሚሻው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ ደስ ፡ ይበለው ።

፬ ፤ ኅሥሥዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወትጸንዑ ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአም